በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

መነባንብ

# አቡነ ጎርጎርዮስ

ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም ሐዋት ቤ/ን አስደንጋጭና እጅግ አሳዛኝ እለት ነበር ይህ ቀን በተለይ ለእናታችን ተዋህዶ ታለቅ የሀዘን ቀን ነበር እንቁ የሆን ልጁን ያጣችበት አሰቃቂ ቅጽበት

ምነው ተዋህዶ የሀዘን ለስበሽ

ምን አግኝቶሽ ይሆን ምንስ ደረሰብሽ

ምነው ጨፈገነነ ያብሩን ገጽሽ

በእንባ ተሞሉ ማራኪ አይኖችሽ

ወዝሽ ደረቅ ነጥፎ እንዲህ ጎስቁለሽ

ከስቶና ገርጥቶ ከዳሽ ሰውነትሽ

ገጽሽ ተቋረጠ የት ሄደ ፈገግታሽ

አረ እስኪ ንገሪኝ እናቴ ሆይ ምን ሆንሽ

ማን አስቀየመብኝ ከቶ ምን አስከፋሽ

የሲቃ እንባ በጎርፍ የሚዘንበው ከአይንሽ

በሀዘን የምትቆምዝሚው እንዲህ ተከራምተሽ

አረ እስኪ ንገሪኝ እናቴ ሆይ ምን ሆንሽ

ችግርሽን ልስማው ጭንቁን ልከፈልሽ

ለምን አለቀሰ ለምን አነባ

እንዴትስ አልብስ ሀዘኑን ከባ

ያ ትልቁ ልጄ መመኪያ ቀኝ እጄ

ጥሎኝ ትቶኝ ሊሄዱ መቃብር ሲገባ

ተስፋዬ መንምኖ ስሆን ህይወት አልባ

ለምን አለለቅስ ለምን አላንባ

ምንም ሳላስበው ሳልዘጋጅበት

ልጄ ወጥቶ ሲቀር እንዲያው እንደዘበት

ፍቅሩን አጣጥመው ልጆቹ ሳይጠግቡት

ህልሙ እውን ሳይሆን ሳይፈጸምለት

ሊረታ ሊረታ በዚያ በአይቀሬ ሞት

ማልቀስም ሊያንስብኝ ነው ደረቴን መደቃት

ኡ ማለት መጮህ የደም እንባን ማንባት

ጎርጎርዮስ ልጄ እያልኩኝ መጣራት

ስራውን መዘከር የእርሱን ታላቅነት

ግና . . .እንዴት ይፋለኛል የእርሱን ነገር ማውራት

ታሪኩን መተረክ ዝነውን ማግኘት

› ብቻ ትንሽ ልበል አንዴ ፍሬ ቅንጣት

ልጆቼን ሰብስቦ ሊግታቸው ወተት

ዘሩን እየዘራ የወንጌልን ትምህርት

ታታሪው ገበሬ ያለው ትልው እውቀት

አርቆ አሳቦ አስተዋዩ አባት

ማዘዝን የማይወድ ለብዙ ሀብታት

ጭቃ ድንጋይ ሳይል የሚተጋ ለመስራት

ደካማን የማይንቅ የሚለግስ ብርታት

ስርአትን አክባሪ ያለ አንዳች ማመንታት

ለፍቅሩ ዳርቻ ወሰን የታጠለት

የጎስቁሉን በበደል በሀጢአት

የተዘፈቁትን በጨለማ ህይወት

መርከብ ሆኖላቸው ከገደል በማውጣት

ንጽህና ቅዱስ ያላቸው ስርአት

እንዲሆኑ ሊያደርግ የእምነት ሊቃውንት

ኑሮዋቸው እንዲጎበኝ በእግዚአብሔር በረከት

ሊያደርግ የነበረ ያንን ታላቅ አባት

ጎርጎርዮስ ልጁን እሱን ነው ያጣሁት

ፋና ወጊ ዘወትር አገልግሎት

ሻማ ሆኖ ሊያቀጥል መንገድ ጠፋበት

በጥርጥር መንፈስ ልበኑ ቢታወክ ለተረበሸበት

ቀንበሩን ተጭኖት ሸክሞ በዝቶበት

ማረፊያውን ሊሳየው ያቺን የሰላም ቤት

የነበረውን ልጄን ጎርጎሪዮስ ልጄን

እርሱን ነው ያጣሁት

ምነው ተቻኮለ መቃብር ለመግባት

ስራውን ሰይቋቸው በጅምሩ ትቶት

ህልሙ እውን ሳይሆን የነበረ ምኞት

የዘራትንም ዘር ፍሬዋን ሳይቀምስለት

እንደ ምን አስችሎት ጎኑ አረፈለት

ዝም ብሎት ተኛ ስራ እንደሌለበት

እናንተን ከሰማ አረ እስኪ ቀስቅሱት

ምስኪን እናትህ ታለቅሳለች በሉት

ሀዘኑ ከብዶን አልቻኩም መጽናናት

ግና . . .መጽናናትን ባልችል ሀዘን ቢበዛብኝ

በአጭር ግዜ ውስጥ እርሱን የሚተካ

ልጆቹ ደርሰዋል እኔን የሚያጽናናኝ

አይዞሽ እማምዬ አሰንልሽ የሚሉኝ

እንባዬን አብለው ለእኔ የሚቆምሉኝ

የጎርጎርስ ፍሬ መጽናኝ የሚሆነኝ

አዎ ብዙ አሉኝ ብዙ ልጆች አሉኝ

በአለት መሰረት ላይ እርሱ መሰርቷው

ጽናትና ትጋት ስላለተማራው

የእኔነትን ስሜት ስላስባቸው

ይኸው ይታያሉ የጧፍ  ብርሃን ሆነው

የእናታቸውን ቤት ቅጥሩን አስረክበው

ደንብና ስርአቷን ለአለም አስተዋውቀው

የወንጌልን ትምህርት ለሁሉም አደርሰው

የአባታቸውን ቃል አደራ ጠብቀው

ይኸው ይታያሉ እንደ ጸሐፊ ደምቀው

ወረት የማያውቀው የዘርም ልዩነት

ለወገኖቹ ሲል የሚሆን መስዋእት

ደጅ ሰላም የሚያድር ቃሉን ለማስመት

ለሁሉ የሚያደረስ የወንጌል በረከት

ብርቱና ጠንካራ ያለው ታላቀቅ ትጋት

ተንከባከቢያቸው ወዳጅ የህጻናት

የስጋን መከራ ክስንም በመፍራት

ወደ ኋላ የማይል መልካምን ከመስራት

እንዲቀርቡኝ ሊያደርግ ልጆቼን በመጥራት

ደንብና ስርአቴን ቀኖናዬን ሲያታት

ከትኩቶ አርሞ እንዲያገኙ ብርታት

እንዲጎናጸፊ ቅናትና ጽናት

ጠላቶቼን ሁሉ አንገት በማስደፋት

እፎይ ብዬ እንድኖር ያለ ምንም ስጋት

ያስቸለኝን ልጄን እርሱን ነው ያጣሁት

አረ እንዴት ልጽናና  ላግኝ ሰላም እረፍት

የሚያርፍበት አጥቶ አይኔ ሲንከራተት

ድምጹ ሊናፍቅ ሊሳነጥኝም መስማት

ማልቀስም ሲያን ሰኝ ነው ደረቴን መደቃት

አ ! ማለት መጮህ የደም እንባን ማንባት

ጎርጎርዮስ ልጄ እያኩኝ መጣራት

የነ አትናቴዎስ የአባቴቾን ትምህርት

መማር ብቻ ሳይሆን ያሳየ በመስራት

እነርሱን በመምሰል በምግባር በሃይማኖት

አደራ ጠበቂ ድካም የሌለበት

የቁርጥ ቀን ልጄ እኔ የምመካበት

ለልጆቼ ጽናት የሆነ መሰረት

መነኙ መነኩሴ የቆ እውነት

ለቅርስ ታሪኬ ያለው ታለቀው ቅናት

ደራሲና መምህር የእውቀት ስለ አባት

መምከር መገሰጽ የዚህን መጽናናት

ልማዱ የሆነ ችግረኛን መርዳት

ኑሮት ያስተማረ የብትህውና ህይወት

መጽህፍታት ድሮ እንዲጠቀሙበት

ከትውልድ ትውልድ እንዲያስተላልፉት

ለምግባር ለሀይማኖት እንዲሰጡ ትኩረት

ይህን ሁሉ ነገር ያደረገን አባት

ጎርጊዮስ ልጄን እሱን ነው ያጣሁት

ያንን ታታሪ አባት የጽናት ተምሳሌነት

ጎርጎርዮስ ልጄን እሱን ነው ያጣሁት

ሀዲስ ሀዋርያ ፀጋው የበዛበት

ልጆቼን ጠባቂ ከጥፋት ከክህደት

ከተኩላው ሸንገላ ከእሳት አንደበት

ሊያዮት የሚያስተምር ሳይናገር ቃሉ

ታዲያ ------ለምን አለቅሳለሁ ለምን አነባለሁ

የሀዘንን ከባ እከናንባለሁ

ልጄ እኮ አልሞተም ተግባሩ ሀያው ነው

ፍሬውም ጎርምርቷል በእምነት የዘራው

ህልሙም እውን ሆኗል ባይመለከተው

ስለዚህ ሀዘኔን ልተውና

የሰላም ከባዬን ልከናነብና

በልጆቼ ትጋት ለጋጥ እንደ ገና

ሰላም እረፍት ያግኝ በእነሱም ይጽናና

መቅደስ አያሌው

## ደ/ብ/ቅ/ገብርኤል ቤ/ክ

## ሠ/ት/ቤት

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**

**መነባንብ**

**እሱ እኮ ነው**

**እሱ እኮ ነው የህይወት ቃል**

**ቃሉ የማያልፍ የማይታበል**

**ጥንትም ያለ የነበረ**

**አለሙን በጥበብ የመሰረተ**

**ምድርን በሀይሉ የፈጠረ**

**ነቢያትን ያናገረ**

**ሀይል ሱባኤ ያስቀጠረ**

**ከይስቅ ጋር የሰዋ**

**እስራኤልን ያስከበረ**

**ከዮናስ ጋር በአሳ ሆድ**

**ከዮሴፍ ጋር የተሰረ**

**እሱ ነው ለሙሴ**

**ህጉን ትእዛዙን ያስተማረ**

**በተረዳ ሶስትነቱ**

**የሚመሰገን በፍጥረቱ**

**በህልውና በመለኮቱ**

**በአገዛዝ በጌትንቱ**

እሱ ነው እሱ የጥንቱ የጥዋቱ

እንዘ አሀዱ ሰለስቱ

እጽብ ብቻ ይወስናል

ቀዳማይ ልደቱ

አይመረመርም ረቂቅ ነው

ዳግማዊ ሰውነቱ

ግሩም ድንቅ ነው ጥበቡ

ወሰን የለውም ቸርነቱ

ወልደ-አብ ወልደ ማርያም

የሰማዩ መሬቱ

እሱ ነው እሱ አልፋ አሜጋ

የሰማዩ መሬቱ

እሱ ነው እሱ ነው አልፋ ኦሜጋ

የሚታዘዙለት መላእክ

የአለም መድሀኒቱ ስጋዌ

ረቂቅ ነው ምስጢሩን

ቃል ከስጋ መጣመሩ

ያለምአወክ ሰው መሆኑ

መቀላቀል ማደሩ

በፍቃዱ በግብሩ

እድ ሆኖ መዋቀሩ

በተዋህዶ መኖሩ

ሰው አምላክ ሆኖ መክበሩ

እሱ እካን አይል ጥበበኛ

እጽቅ አይል እውነተኛ

እነግስ አይል በዙፋኑ

አክብር አይል ባለ ዙፋኑ

ዘላላማዊ ሀይል አምላክ

የማይወሰን በቦታ

እሱ ነው እሱ ሳንፈጠር የሚያውቀን

እንዲያው በጽድቅ የጎበኘን

በፍቅር ተሰቦ ተጓዳ

ሰማያዊ መሬት ወርዶ

ስጋ ለብሶ ተዋህዶ

የከበረው ተዋህዶ

በአሮጌ ጨርቅ ተጠቅልሎ

በጎላ እንሰሳ ተጠሎ

ከፍጥረታቱ ጋር ያደረ

እሱ ነው እሱ የኛ ተስፋ

ሞትን በልደት የሻረ

የፈጠረውን ስጋ ለብሶ

በህግ ተከሶ ተወቅሶ

እሱ ነው እሱ የታረቀን ተመላልሶ

እኛ በበደልን እሱ ክሶ

እሱ ነው የበጎች መረጠኛ

ኖላዊ ትጉህ የማይተኛ

የደከመውን አጋዥ

የታመመውን ፈዋሽ

ምናለ ከእኛ እሱ እሚሆን

አሮጌው የክብር ይገሰን

# አበው ይናገሩ

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን**

እስኪ ቀስቅሱአቸው አበው ይናገሩ

በሀይማኖት መጽናት ምን ነበር ምስጢሩ

የክርስትና ህይወት ምን ነበር ተግባሩ

መቃብሩን ክፈቱት አበው ይመስክሩ

እኔስ ሰው ናፈቀኝ የሀይማኖት ጀግና

ወልድ ዋህድ ብሎ በእምነቱ የፀና

ምግባር ሀይማኖቱ በእጅጉ የቀና

ሠማእታት በመንገዝ በተነጠቁት

ሐዋርያትም ቁልቁል የተዘቀዘቁት

ቅዱሳን በእሳት የተለበለቡት

አባቶች በገዳም ደርቀው የተገኙት

እኮ ለምን ይሆን ? ምን ነበር ምስጢሩ

እስኪ ቀስቁስአቸው አበው  ይናገሩ

በሀይማኖት መጽናት ምን ነበር ምስጢሩ

የክርስትና ህይወት ምን ነበር ተግባሩ

መቃብር ክፈቱና አበው ይመስክሩ

ይናገር ዝቋላ ግሸን ላሊበላ

የቅዱሳን አጽም ለምን እንደበላ

ዋልድጋም ይናገር ደብረዳሞም ሳይቀር

እንባቸው መፍሰሱ ለምን እንደነበር

ፈልገው ይሆን እንዴ በከንቱ መሞት

ነፍሳቸው ለሳት ፍጹም እስከ መስጠት

ፀንተው የተገኙት በአንዲት ሀይማኖት

አረ ሰው አማረኝ የሀይማኖት ጀግና

ወልድ ዋህድ ብሎ በእምነቱ የጸና

ምግባር ሀይማኖቱ በእጅጉ የቀና

ጎበዝ ሰው አማረኝ አይኔን ጀግና አማረወው

በእምነቱ የፀና የት ነው የማገኘው ?

በመሰል ከተማ ባራዳ ውጥ ነው ?

ወይስ በዝቋላ በደብረ ሊባኖስ በደብረ ዳሞ ነው

በጎቹን ከተኩላ ነቅቶ የሚጠብቅ

መከራ ቢገጥመው የማያፈገፍግ

እንደዚያ እንደ ጥንቱ ይገኛል ወይ ዛሬ

ወይም ቀስቅሱአቸው አበው ይናገሩ

በሀይማኖት መፅናት ምን ነበር ምስጢሩ

የክርስትና ሕይወት ምን ነበር ተግባሩ

መቃብሩን ክፈቱት አበው ይመስክሩ

የወገን ዘመድ ጥቅሙ ያላማረው

የመናፍቅ እጅ ኪሱን ያልዳበሰው

የአለም አሻንክላ ልቡን ያልማረከው

የክርስቶስ  እርሱ ጀግና ማነው

ምስጢርን ከምስጢር አንድ አርጎ ተምሮ

ወልድ ዋህድ ብሎ እምነቱን መስክሮ

እንጦስን መቃርሶን በልቡ ያኖረ

ከጳውሎስ ከቂርሎስ ጥበብ የተማረ

እውነት ጀግና ማነው ጠላት አሳፋሪ

ወልድ ዋህድ ብሎ እምነቱን መስካሪ

ፈረሃ እግዚአብሔር በልቡ ያደረ

ቤተክርስቲያንን ያልተደፋፈረ

የት ነው የሚገኘው ለሀይማኖቱ ሚኚ

ለተዋህዶ እምነት ጠበቃ ተሚጋች

የወገን መመኪያ የከሀዲ መቅሰፍት

ማነው እርሱ ጀግና ይነሳ ቀስቅሱት

አልያም ቀስቅሱአቸው አበው ይናገሩ

በሀይማኖት መፅናት ምን ነበር ምስጢሩ

የክርስትና ሕይወት ምን ነበር ተግባሩ

መቃብሩን ክፈቱት አበው ይመስክሩ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# ምን አለበት አሉ

ኦ ምን አለበት አሉ ምን የሞላባቸው

ዘመን ያመጣችው ጊዜ ያፈራችው

ትርጉሙን ታውረው ያሬድ አባታቸው

አንሞዝቅ አሉ በዘፈን የጠማቸው

ማህሌት ምስጢሩ ግራ ሆኖባቸው

ዘፈኑ ዳንኪራው ሱስ የሆነባቸው

ግእዝን ለማሰማት እምቢ አሉ ልባቸው

ፋ ተዋህዶ ውብ መጠሪያሽ

ፍቅር ነበር ላስተዋልሽ

በምናልባት ጀርባው ቆስሎ

ጤት ይቀየር ይታደስ ብሎ

አረም በቀለ ከአውሮፓ ዝሎ

ጥርሱን አግጥጦ አይኑን ጉልግሎ

ነቅለሽ አስወጭው ሳይጨርስ ገሌ

ኦ ሰይጣን በሸመቃ አይናቸውን ጋርዶ

ጊታር ውስጣቸወን በዳንኪራ ወስዶ

ያስጨፍራቸዋል  አንድዶ

ያጨልማቸዋል በዳስ አስገድዶ

ፋ ጆሮአው ተደፍኖ መልካሙን ከመስማት

የገዛ አእምሮአቸው አሸንቸው ሀጢያት

በምድርም በሰማይ በጥፋት ላይ ጥፋት

ኦ ኦርጋን ፒያኖን ሁሉን አሙጠና

ኦፐራ ነው አሉን የዳዊት በገና

የዘመኑ ወጣት ምን አለበት ትውልድ

ግራውን መረጠ ጠማማውን መንገድ

ተዋህዶ እኛ የአንቺ ልጆች በጥላሽ ስር ያለን

የሴማው ባለቤት ሊቁ አባታችን

ደጉ ቅዱስ ያሬድ አለ በውስጣችን

ኦ ወጣት ሆይ አስተውል ሳትረዳ አትማ

ወደ ስጋ ፈቃድ መሄድ አትሻማ

በሀጥያት ተገዘህ ቆስለህማ አትድማ

ወደ ስጋ ፈቃድ መሄድ አትሻማ

በሀጥያት ተገዘህ ቆስለህም አትድማ እናትህ ስትመክርህ ኧህ ብለህ ስማ

የጠራችህ ሃይማኖት ንጽህ ሀብት ይዘህ

እያለህ ልመና ለምን ትገዛለህ

ቤትህ ትረፍርፍ ምስጋናው ሞልቶልህ

ብር ለመበደር ለምን ትሄዳለህ

ኦ ስለዚህ ወገኔ ያሬድ እኮ አልሞተም

ህያው ፍሬው አለ ትላንትናም ዛሬም

ተዋህዶን ጠብቅ በርትተህ ሁሉ ጊዜም

ምን የኦሪት ቤት መስ ብትታይ

ጥበብ ምስጢር አዲስ ነው ምንጊዜም

ጣፋጭ ኖት ዘወትር መጥተህ ብትሳለም

አልፋና ኦሜጋ የዋጀልን በደም

ይልቅ ሊታደስ ዛሬ የሚገባው

በሀጢያት ያደፈው የእኛ  ልቦና ነው

ለእግዚብሔር መንግስተ የምንታደለው

እህቲ ሀይማኖትን ብለን ስናምን ነው

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

**በህ/ክ/ኪ/ጥበብ**

**ከግሩም ግርማ**

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን**

**ኑ እንወቃቀስ**

**ኑ እንዋቃቀስ እንማከር ይላል ጌታ**

**ያሳለፍነው ክፉ ስራ እንዲያልፈው በይቅርታ**

**የመንሰፍ ስጦታ እንዲያድለን የማታ ማታ**

**የተወያየነውን ሳነተረጉም ቀርተን**

**ሰንበት ት/ቤቱን ለማሳደግ የተባበልነውን**

**በሰአት እንግባ ይጀመር እንቅስቃሴአችን**

**ብለን የተወያየነውን በስራ አንተርጉም ተባብረን በፍቅር**

**የምንሰራውን ስራ የምናደርገው እንቅስቃሴችን እንዲያምር**

**መሀላችን ገብቶ እንዲያሳስን ቸሩ እግዚአብሔር**

**ሰማችሁ ወንድሞቼ**

**አዳመጣችሁ እህቶቼ**

**ኧረ አሜን ኧረ ተው ውጣ ገባ**

**ማፍራት ያስፈልጋል በቅለን እንዳበባ**

**አብበን ፍሬ ለመስጠት ስንችል እንደተክ**

**ሰምተን እንዳልሰማን ቁጭ በለን ከመሀል**

**የተወያየነውን እንኳን መተርጓም አቅቶን**

**ይታዘባል ጌታ ሆኖ መሀላችን**

**ምንም ሳንሰጥ ፍሬ ምንም ሳናፈራ አለፈ ጊዜአትን**

ኧረ ተቃጠለ ተቀጠረ አለፈ ጊዜአችን

በወጣትነት ጊዜ ሳያብብ ፍሬአችን

በስነ ጽሁፍ በድራማው  ወጣ ገባ ስንል

እንዲያው ቆመን ቀረን ሳንገባ ከመሀል

በርቱ ተበረታቱ ይላልለ  አምላካችን

ለፍሬ ብቁልኝ ይለናል ሁላችን

በርቱ ክፍ ብሎ አንድ ላይ አንሁን

ተነሱ እንነሳ እንበርታ ሁላችን

አንዱ አንዱን ያንሳ ይበርታ ክንዳችን

ክንዳችን ቃሉ ነው የህይወት መድህን

መመርያው ማበብያው እሱነው ይላል አምላካችን

ስለዚህ ስማኝ ያዘው ተከተለው አጥብቅ መመርህያን

ወቀሳ መልካም ነው ያውም የአባት

ሳይሞቱ እዚህ ሳሉ ዳግም በመሬት

ከቶ ያስፈልጋል የጌታ ምህረት

አሥ ተዋቀሱ ኑና ቃሉን ስሙ

መውጣት መግባታችሁን አንድ ላይ አርሙ

በህይወት ቃል ሆናችሁ ይለናል ተስማሙ

ለመንገድህ ካርታ ለጭለማ መብራት እባክህ አድርገው

ለመንፈስህ ፍሬ ለህይወት ዋስትና እንዲሆንህን አኑረው

በቃሉ ተማሪ በሀይማኖት ጽና በአእምሮሽ አኑሪው

በምድራዊ ደስታ ፍጹም ተውጣችሁ

መምጫው ቀን ሲመጣ እንዳይቸግራችሁ

ሰው ቢበድላችሁ በደለች አትበሉ

በቀል አትጣራ አትገዳደሉ ነ

ምን ቢጠላችሁ ጠላትን ውደዱ

ለአንድ አምላክ ፈጣሪ ለእግዚአብሔር ሰገዱ

ከሰው ተፈቅራችሁ ድንገት ብትጣሉ

ቂም አትያያዙ ይቅር ተባባሉ

ነድያን ቢመጠዩ ትንሽ እርዱን ብለው

ፊት ማዞር ተውት ከላችሁ እርዷቸው

ፈጣሪ ካላመን አይጠፋም ፊቱ

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

# ምነው አለለወጥ አልሽ

ምነው አለለወጥ አልሽ የኔ ህይወት

በጌታ ቃል በሱ ቸርነት

በተማርሽው ቃል በህይወት መሰረት

የጌታን ቃል ትእዛዙን ሽረሽ

በሱ ታድነሽ ታየሽ

እንዲያው ዝም ብሎ አልነበተሽም

ታድያ መች ነው የምትቀየሪው

እንደ ወንድሞችሽ የምትሆኚው

እንደ እህቶችሽ የምታብቢው

መሀል ቀለል ብለሽ የምታፈሪው

ከፍሬ ታጅበሽ የምትዋቢው

እኮ መች ነሽ ተናገሪ

የበላሽበትን ውጭት አትስበሪ

በመንፈስ ሳትመላለሽ ቀርተሽ

ሁል ጊዜ ስትመላለሽ ስጋን አዳልበሽ

አሁን ግን ታሮሽ ጌታ ፊት ቀርበሽ

ታድያ ተናገሪ እኮ መስክሪ ምን ትያልሽ

አልለውጥ ነው የምትይው ወይስ አልቀየር

አመለበጥ ነው የምትይው ወይስ አልሰበር

ማንነትሽን ያውቀዋል የፈጠረሽ እዚአብሔር

አንዴ ይዞሽ መጥቷል ወጭ አጠይልሽ ከሀገር

ሁሉም የሱ ነው ይልቅ ራስሽን ጣይ ከምድር

አንድ ቀን ጴጥሮስ ከባህር ዳር

አሳ ለመያዝ ሂዶ ሀዋርያትን በርትቶ ከሰፈር

ሁሉም ደካሙና አሳ ከመረቡ ሳይገባ

በጣም ዛሉ በጣም ደከሙ ሆዳቸው ባባ

ከዚያ ቀረበና ጌታ በመርከቡ

የሚበላ ጠየቃቸው ምንም እንዳያስቡ

እነሱም መለሱ የለንም የሚበላ

ከትላንቱ ዛሬ በፍጹም ሰንደክም

በጣምም ዝለና በፍጹም አልያዝንም

ብለው መለሱለት በጣም በማሳዘን

ብሎ ተናገረ በስተቀኙ ጣሉት መረቡን

እነሱም እሺ አሉ በቃሉ በመተማማን

ከዚያ ቡሀላ በመረቡ ሞላለቸው

ያላገኙትን ስላዩ በጣም ደስ አላቸው

ከዚያም ጴጥሮስ መጣ ጌታን ሲያይ ከባህር ዳር

እሱ መሆኑን ስላወቀ ፍጹም ሳያማርር

ጴጥሮስ ተለወጠ በጌታ ፊት

ትላንት ሲክድ በፊት ለፊት

አሁን ግን ተለወጠ በምህረት

ይህንን ምሳሌ ተመልክተሽ

ባንቺ መመለሱን መሆኑን ተረድተሽ

እውነቱን አይተሽ ሁኝ የተሰበርሽ

ታድያ መቼ ነው የምትለውጭው

ራስሽን አውቀሽ በጌታ ፊት የምትታይው

ደካማ መሆንሽን የምትናገሪው

እኮ መች ነው ተናገሪ

የበላሽበት ውጤት አትሰበሪ

ስለ ስጋሽ ትተሽ በለ ነፍስሽ መስክሪ

ታዲያ በየትኛው ነው ያንቺ መቀየር

እስቲ ተናገሪ ሆነሽ በፍቅር

መቀየሩ ለራስሽ ነው

አንቺ ነሽ የምትጠቀሚው

ባትኖሪበት እስከ ወዲያኛው

ስለዚህ ንስሃ ግቢ ራስሽን ስጭ ለጌታ

እንዲያስብሽ እንዲያነሳሽ የማታ ማተ

እንድትሰለፊ በቀኙ ሆነሽ በተርታ

እባክሽ ማሪኝ በይው እንዲያደርግልሽ ይቅርታ

**ወሰስብሐት ለእግዚአብሔር**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# አደዞሽ እናት አለም አትዘኝባቸው

አይክፋሽ አያሳዝንሽ

ዛሬ እኛ ብንክድሽ

እኛ ብናቋሽሽ ብንጠላሽ

ቃልሽን ሰምተን ብንጥለው

ጥበብ ምስጢርሽን ብናጎድፈው

እውነተኛ የወንጌል  ምንጭሽን ብናደርቀው

በውስጥሽ ተሰግስገን ብናጎሳቅልሽ

ለጠላት አሳልፈን ብንሰጥሽ

ሰምተን እንዳልሰማን ሆነን ብናለፍሽ

አታልቅሽብንም እናታለም አታዛኝብን

እኛ ------ብንሸሽ

እኛን ሳትጠሪ ባንሰማሽ

መጡ እንገባሽን ሊያብሱ ልጆችሽ

በእውነት የወለድሻቸው ከአብራክሽ

ቃልሽን ሰምተው በእውነት የቆሙልሽ

በእውነት ምግባር የመሰከሩልሽ

መጡ ዳግም ሊናገሩ ታሪክሽን

መጡ ሊያስተውሱን ሊነግሩን

የጥንት የጥዋቱን ሊያስታውሱን

የኛ መክዳት አሳዝኞን ሊያጽናኑን

የኛ ባድነት ሲነግሩን እውነቱን ሊያሳዩን

ሳንሞት ሞተን ለቀረነው

በለያችን የሀጢያት መቃብር ለተገነባው

አትዘኚ እነት አለም

አታልቅሽብን

ይበቃል የፈሰሰው እንባሽን ጥረጉ

የለበሰሽውን ማቅ አውልቂ

የፍትሽን አመድ ጥረጊ

ምንም ታጥቦ ጭቃ ቢሆንም ስራችን

አለንልሽ በማለት አይደፍርም ቃላችን

እውነት ከደቶናል ከለያችን

እናት አለም

እናት አለም ዳግም ማቅ እንዳናለብስሽ

ቃልሽን ለትውልድ እንድናደርስልሽ

ከቤትሽ እንዳንጠፋ ልጆችሽ

በእውነት እንዳንመላለስ

ያለፈውን ይቅር ባይ

ለአሁኑ ጠብቂን /2/

እመኝን እናት አለመ

ዳግመኛ አናስከፋሽም

አናሳዝንሽም

ሰማን እስጢፋኖስ ሊቃ ሰማእታት

ሳትጠራ የመጣህባት እናትህ በእውነት

ቆመህ መስከርክላት እንደ ጥንት

አስታወስክላት ለከዳት

ለኔደ ከቤቷ ጥሏት

ነገርኮላት አሳሰብክላት

ዳግም እንዳናስከፋት እናትህን

ይጠብቀን አጽም ጸሎትህ

ይርዳን እስከዘላለም

ቃልህን እንድናሳውን ለትውልድ

እንዳንጠፋ እናትህ እንዳንክድህ

ሰማን አትናቲምስ እናትህን ብናስቀይም

ቃልህን ሰምተን  ትዛዝህን ባንፈጽም

አትዘንብን በኛ በልጆችህ

ሀጢአት ላደከመን የጽድቅ መንገድ ለጠፋን

በእናትህ ላይ ማቅ አመድ መጨመርን

ይቅር በለን ተማጽነናል በቃልህ

ዳግም አናስከፋም ልጆችህ እናትህ

ዲዮለቆሮስም አትዘንብን

የሀይማኖት ፍሬ ይህ ነው ብለን ሰጠኸን

እኛ  ግን ለወጥነው በጥቅም ላይ ነን

አትዘንብን ዲዮቆሮስም ብናስከፋህ እናትህ

ዳግመኛ ከረፋክባት ብንቀሰቅስህም

ተመጽነንህል በረገፍው ጥርስህ

ዳግም እንዳንቀሰቅስህ

አትዘኝብን እናታለም

ተማጽነንብሻል በልጆችሽ

በዲዮስቆሮስ በአትናቴናስ

በአስጢፋኖስ

አትዘኝ እናት አለም

አታልቅሽ ----------

በቤዛ ብዙሃን ኪዳነ ምህረት ሰንበት ት/ቤት የተደረሰ

ደራሲ በኪ.ጥ.ማ

18/03/1989 ዓ.ም



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን




እኔ ፈላስፋው አዶንያስ ውሸት ----------

ሰዎች ያሸብኝን የእውነት አርበኛ ነኝ

ሀሰትን እረግማሁ ኮንናለሁኝ

የእውነት ሀገር ለማወቅ

ከንጋት እስከ ጸሐይ መጥለቅ

ስመራምር መቋጫዬን ስላገኝ

ከእውነት መስክ እስክል ደረስኩኝ

ዛሬም ወደ እርሷ ሮጣለሁኝ ገሰገስኩኝ

እውነት አሸንፋ ለአለለም ብርሃንና ፈንጥቃ

ሰነፎች ርቀው እርሷ ርቃ

ማየት ነው የእኔ ምኞት

የሀጥያት ጥፋት የሀሰትን ሞት

ግን ለምን አዶንያስ አላችሁኝ አገሩን አምሳ

የእርግማን በደል በእኛ ላይ አፍስሳ

ድሃ ተበደለ

ፍርድ ተጓደለ

መበልቶች በረሃብ አለቁ

አዛውንት ጠምር አግኝተው በሞት ተነጠቁ

ባለጸጋው ጠግቦ ሲንሸራሸር

ረሀብተኛው ፣ ህመምተኛው ከአልጋ ሰቀር

እንባ ፣ ዋይታ በምድር ሲደርስ

የሀዘን ጠል ምድርን ሲያረሰርስ

እንዴት ዝም ጭጭ ልበል

የእርፍ የሰላም ውሃ ጠፍቶ ነገደ አዳም ሳይቃጠል

ቀስቅሳ ተናጋሪ መስክር

የሚያሳኝ ነገር

ይኸው ይታያል ከፊቴ ደንቅሮ

ስጋ ስትሮጥ ከመከራ ለመሸሽ ወደፊት

ነፍስም የሰማእታት ክብርን ለማግኘት ስትከንፍ

ግን እብድ አይደለሁም እኔ አዶንያስ

የእውነት ባሪያ አረመኔዎች የምኮስ

መጽሐፍትን እቃርማለሁ

ምስጢር ላይ ለመድረስ ስፈልግ ተስትዬ ገሰገስኩ

እኔ መርምራለሁ

ጥበብንና እውነትን እሻታለሁ

ገንዘብዬን አኳትንም

ስራ አጣሁ ብዬ አልቦዝንም

የሰው ልጆችን ድህንነት ምስኪን መርምሬ

በድርሳነ ጥበብ አስፍሬ

የእውነት ባላ ጋራ እንዳለ

ሰነፍ ለሀጥያት ባህር ላይ ዋለለ

ፍቅር ከመለኪያው ሚዛን አንሶ

ተንኮል አሸቅቦ አለመንወርስ

እውነት ታርዞ

ጥበብ እርቃን ኑ ተመላልሶ

ጸጋናማ ለተዋልዶ ቅድቅ መጣችሁ

ፍርሀት ችግር ከላባቸው

የእውነት ብርሃን በሀሰት ጨለማ ስትዋጥ

በአናብስቱ ተንኮል ስላመጥ

እንዴት አይቼ አልፋለሁኝ

ቃልን ለስውር አስተጋባለሁኝ

አዶንያስ ፈላስፋው የእውነት ሀዋርያ ነኝ

መሰክራለሁ አስተምራለሁኝ

አለም በጨለማው ውሰኝ ነው ያለው

ብርሃን ያስፈልገዋል ለሚለው

እኔመሰክራለሁ

ስለ እውነት ዝም አልልም እናገራለሁ

የተቀጠረለት ቅጥራፍር ሰባት

ሁሉም መመለሻው አደረጋት

መላልሰው ረገጧት

ሰራዊት አዝምታ ወጓት

በድ ሆኖ እንድትሆን ተሰለፈባት

አቃጥለው እንድደው ልጨርሷት

የእሳት ሲደድቀቁባት

እርሷ ግን ብርቱ ናት

ሁሉንም በጥበብ በማስተዋል አሸንፋ

ከዘመን ዘመን አልፋ

ትገስግሳለች በዘመን መኩራኩር ተሳፋሪ

ጠላቶቹን እህቴ ነሽ በላት

ወዳጄ ብለ ጥራት

እውነተኛ ማህቶች

ለአለማችሁ አበሩላት

ፈልጋለሁ እውነተኛ አማኝ

በሁሉ አምል

እውነት ጨለማው ደባብ ጋርዷት

አላያት ሁሌም ብሩህ ነኝ

እውነተኛ ሰው ግን አለፉ ፈልጋለሁኝ

እስኳገኝ ድረስ ሳትናለሁኝ

ከደንያስፈላስፉ ነው ባዮች

እባካችሁ ደቂቃ አዳም ተመከሩ ሰዎች

# የእማሆይ ዘፉግት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

እማሆይ ጣዲቅ በጠዋት ተነስተው

መቁጠሪያ ሲቆጥሩ ከደጅ ተቀምጠው

ጸሎት ሲጸልዩ አቡነ እያሉ

ወደ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ሲሉ

የጥንት ጓደኛቸው አብሮ አብሮ አደግ እታቸው

በቆብ ጊዜ የነበረ ክብራቸው

መጡ ምስጢር ይዘው ወደ እማሆይ ዘንድ

እንዳይሆኑ አበብው የነፍስ በላ እዳ

እንዴት ዋልሽ ጠዲቁ አሉ በጥንት ዘዬ

ገብተው ሊነግሱት ከልባቸው ቀይ

አጣመጠው ቀረቡ ቃላት አሳምረው

የጥንቱን እማሄይ ክቤን ተመስለው

እዚሃር ይመስገን ክብር ለፈጣሪ

ከዚህ አድርሶኛል ለሰይጣን ጧር

አሉና እማሆይ የጥንቷን ክብነሽ

በአርምሞ አዮአቸው ሊሆኗቸው ከሳሽ

እማሆይ ክብነሽ የጥንቷ ጓዳ

ምነው ግራ ገባኝ አረጀሁኝ እንጂ

ወየት አለ መቋሚያሽ ድጋፍ ያደረገሽ

ቆብ መቁጠሪያው ወዴት አደረግሽው

በጉዬ መጣሁ ነው ወይስ ተላላቅኩ

ሳይገባኝ ሚስጢሩ በቅገሮት ዘባረኩ

እያሉ እማሆይ ግራ እያገባቸው

ክቤን ያዬ ጀመር በጥልቅ አስተውለው

ዳግም በለሆሰስ እንደዚህ ቀጠሉ

ለራሳቸው ብቻ በሚለማቀሉ

ኧረ አልተሳሳትኩም እርሷው ከቤ ናት

ጸጋዋን ምን ገፎ እንዲህ አሳስቆላት

እያሉ አምድ በጣም ሲጨነቁ

ግራ ቢጋቸው ነገሩን ሲያውሉ

የጥንት እኛቸው ቀቢጠኛ አሉና

እኔው ጓደኛ ነኝ አትጨነቂ

ቆቡም ወልቋል በቃ ተቀምጧል ቤቲ

የጥንቱ ሞኝት ቀርቷልና ሰምሮ

አዲሰ ሰው ሆኛለሁ ሰፊ ቀኔ ሰምሮ

ለእኔ የደረሰኝ የምስራች ቃል

ለብቻው ዳነች ንፍግ እንዳልባል

እህቴን ልቀስቅስ ከተኛሁበት

ልምራሽ መንገዱን ልውሰድሽ እቤቱ

መጣሁኝ ወደ አንች አብረን እንድንሆን

አንድ ሆኖ እንዲቀጥል የጥንቱ መንገዳችን

ብለው ሲናገሩ የጥንቷ ክብነሽ

ይሻለናል ከቆብ ይልቅ ነሽ

እማሆይ ጨንቋቸው ምስጢረ ርቋቸው

ያወሩ ጀመረ ከውስጥ ከራሳቸው

ምን ሚስጂ ይሆን ይህች ሰው ምን ነካት

ክብደት ታልሆነማ መርቋሚያ የሚያስጥል

ቆብን አስወልቆ ከአለም ሮሚያዋውል

ምንድን ነው ሚስጢሩ እንዲህ ያናገራት

አለኝ የምትለው የትኛው ነው እውነት

አሉና እማሆይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው

እስቲ የምትይውን ባገልጸጠሽ አስደጂኝ

ምኑ ነው ጥፋቱ ያስቆጠረኝ ከሞኝ

እማሆይ ጣዲቁ ብለው ሲጠይቁ

በነገሩ ክብደት እየጨነቁ

አይ ጣዲቅ እናቴ አንች እንደ ድሮነሽ

ከበፊቱ እምነትሽ ወይም ፈቅ አላልሽ

እኔ ትችዋሁ የቀድሞውን ሞኝነት

ምስጢር ከሆኑብሽ ግልጽ የተናገርኩት

እነሆ ልንገርሽ ልብ ብለሽ ስሚኝ

እኔ ያገኘሁትኝን አንችም እንደታገኚ

ሰባክን ስፓዝን በየገደማቱ

መድን መንገድ ደርሶ አድርሶ መጠጊያቸው

ጌታን ተቀበልኩኝ ዳግም ተወለድኩኝ

ገና አሁን ልጅነት ከአምላክ አገኘሁና

ለካንስ ከንቱ ነበር ያለፍኩት

አማልጁን እያልኩኝ ዙሪያውን የዞርኩት

ጌታዬን ቀጥታ አሁን አገኘሁት

ይልቅስ ተነሽ አንቺም ዳኚ እንደኔ

ይህቆብ አይረባሽም ከንቱ ነው ኩነኔ

ጌታን ተቀበይ ድጋፍሽ እሱ ነው

መንገድ መገናኛ ለአምላክ የሚያደርሰው

እያሱ ክብነሽ የጥንቷ መነኩሴ

› መስዏቸው የደጉ ኂላ ከመወቀስ

እማሆይ ጠዲቁ እጅግ ተከባንበው

ተነሱ ታሉበት ድንገት ተሰፈጥረው

በስመአብ ወወልደ -----አሉ እያማተቡ

በክዘጌ ንግግር ጣነው ሳያስቡ

ሰአሊ ለነ ቅድስት ምኑን አስማሽኝ

ክቤ ሪቂልበኝ ከዚሁ እንዳትቀርሊኝ

ተኩሎች ነፍጠሽ ተበላሽላቸው

አንችም እንደ ሌላው ውድ ቀሽ በምክሪያቸው

ዋ የተብዬ ቆብ ዋዛ ተቆጠረ

ሰው ሁሉ ቆብ ማድረግ መመንስ አፈር

ምነው ክበቤ ምን ሆንሽ ምን አደነዘዘሻ

አንችም እንደ አርቆስ ክህደትን ተማርሽ

ሞተሽ ነበር እኮ ለአምላክ ፍቅር ብለሽ

ምነው መግነዝሽን ከፈኑን ሳትፈቺ

ባታወልቂ ቆቤን በሞት ብትረቺ

ምን አለበት አንዱን ሞት ብትሞች

ምናቸው ስቦሽ ነው በምን አታለሉሽ

ጸጋሽን አርቁታል በደንሽን ያስቀረሹ

ምነው አሉ እናቴ ያለ እናት ያስቀሩሽ

ማህተም የለሽ ተባልሽ ሆንሽ እንደሌለው

በለጠሽ አንችም እንደ ሌላው

ከሃዲ ሆንሽ እኮ አምላክን ---------

አማላጅ ነው ብለሽ ፍጡር ደመረሽው

እማሆይ መባሌ ኧረ ምኑ ከፋ

ማነውስ ሩብ ከፍቱ በነፍሱ የፈጠረ

የተክልዬ ወሰንሽ ቆረጠልሽ ሆድሽ

ሊናገሩ ቢያዩ ክቤ ተደናግጠው

የጥንቲቷ እማሆይ ዛሬ ተለውጠው

መጥፋታቸው ሳያንስ ከክህደት መጓዙ

ሌሎችንም ነፍሳት ከሲኦል ሲያበዙ

ነበርኩ እያዜው ጥንቱን በትዝታ

በዝብ ቃላታቸው ማንንም ላይረታ

የእራሳቸውን እጣ ግፊት እንዲቀምሱ

የእማሆይ ጣዲቂን ልብ ሊያሳሱ

ምነውን ጠዲቅ ለምን ትቆጫልሽ

አናግፊኝ በእርታ በጥሞና ሆነሽ

ስሚኝ እስቲ እኔ ከንቱ ነው ድካምሽ

ራስሽን አዋርጂው መርዶም መጸለይሽ

ወደ አፍ የገባ ሳይሆን የሚያረክሰው

ከእግዚአብሔር የሚያጣላ ክፉ መናገር ነው

ለምን ነው መሞቱ በደም መቀበሩ

ጸልየሽ መኖር ስንችል አንገት ማቀርቀሩ

ጣዲቁ ሞኝ ነሽ መቁጠሪያ ምንድን ነው ትርጉሙ

ውዳሴ ግልጎታ መጣፍ መድገሙ

ይበቃል ካነብብኝ መጽሐፍ ቅዱሱን

ጌታን ተቀበይው እንዲሆንሽ አጋር

እያሉ ክብነሽ ሳይደክሙ ለመርታት

የጥንቱን ማንነት በአንዴ ረስተውት

ይሻለኛል ሲሉ የዲማስ ሞኝነት

ክቤን ለመምታት መቅጣት አስኛቸው

ኧረንልሽ ክቤ ምነው እርከን ዘለልሽ

ከመቼው አውቀሽ እንዲህ መዳፈርሽ

እኔ የእጁ ፍጡር የስላሴ ባርያ

የያዝኩትን ጸጉር አእድማስ መሸጋገሪያ

በእርግት ውስጧስ ይሁን ባንቺ ይምሰል

ነፍሴን በስጋይ ጸሉት ይምእልል

ብትረሽው አንተ እ ከቶ አትረሳም

ንጹሀን ሀይማኖቴን ፍጹም አልለውጥም

ሞቼ ለምን ነበር በቁም መቀበሬ

አንተኝ ነበር ሰማያዊ ክብሬ

ታድያ አሁን ድን አጣሁ ምን ተቸግረው ብዬ

የናቁትን አለም የማዞር ዞር ብዬ

ከቶ ዘነጋሽው አምላካዊ ቃሉን

ተከሎች እንዲመጡ የተናገረውን

የላባ ለምጽ ለብሰው መታየታቸውን

ይልቅስ ስለኔ ተደሙ መጨነቁን

ከጥንቱ ይገፍዋለሁ የተክልዬ ወጉን

ይልቅስ ጸልይ እዳሽ ለዛብሽ

ክብሩ አስጦሎኛል ሲኦል መሳስመረጠሸ

አሁንማ ሂጂልኝ አምርረው ቢቆጡ

ክቢ በመጡባት ተመልሰው ወጡ

ጣኢቄም መጣሉ የሃዘን አንጉርጉሮ

ወደ ፈጣሪያችን አቀረቡ እሮሮ

ምነው ፈጣሪዬ ምኑን አሳማከኝ

እግዚአብሔር በላት መልሳት እቤትህ

ለንስሃ አብቃት በጸጸት ገርፈህ

አሁንስ ፈራሁኝ ለእኔም አስጋኝ

የተከሉ ተንኮል መብዛት አሳሰበኝ

ተቀድሼ እንደ ርክስ እንዳድጥለኝ ክህደት

መልሳቸው ይምጡ ይብቃቸው ጥፋቱ

የከፋ ነውና የሲኦል ቅጣቱ

እያሉ ጣዲቅ ዘለቁ ምክከት

ከምስሏ ስር ወድቀው ለድንግል ሊነግሯት



በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

# ጥሪዉን እንስማ

ልብ የሰው ልብ ይባል

መሰሚያ ይልው ይሰማ

ስማ . . . . .ስማ . . . .ሲባል

ሲነፋ መለኮት

ሲጮህ መለኮት

ሲጮህ ንቃ በለው

ህይወት የአምላክ ጸጋ

እድሜም ለንስሃ

መባሉ ለዚህ ነው

ባሩ ሳይዘጋ

ሙሽራው ተጓድሞ

መንቃት በግዜ ነው

ጥበብ ከእግዚአብሔር ናትና

ከርሱ ያልሆነ ጠቢብ

ሀይልም ከእግዚአብሔር ናትና

በእርሱ ያልተመካ ሀይል

በራሱ ጉልበት ሊደፋ

የአለምን ጌጥ ወግ ሰላም ደንቁ

ጀምበር ሳለልን እንመለስ

እንስማ . . .መለኮት ሊነፋ

ቃሉ በቁመ ላይፈታ

የጌታም ትንቢት ላይቀየር

የቁም ትርጉሙን ስንጠብቅ

መሀል ከተማ ተቀምጠን

ዘንዩ ከየት ሊያጠቃንያ

እያልን በፌዝ ስንራቀቅ

ሊከሰት ጊዜው አሁን ነው

ዘመን ከዘመን አማጥቆ

ተምሳሌት በነባሪ ሀቅ

ይልቅ ጥሪውን እንስማ

የዘለአለሙን ወንጌል

የመልአኩን ስብከት

. . . . . .የፍርድ ሰአት ደርሷልና

እግዚአብሔርን ፍሩ

ክብርጸም ሰጡት

ሰማይንና ምድርንም

ባህርንም የውሃውን ምንጮች

ለስራው ሰገዱለት

ተብሎ ሲጮህ እንንቃ

ግዜ ስላለን እንመለስ

እስማ . . . . .ተገፍተናልና መለኮት

ያድስ እለት ስብራት

የምትሸረት

የህይወት እድሳት

በአድስ ዘመን በአድስ እለት

በጠዋት በንጋት

ለብዙ አመት

ለብዙ ዘመናት

ጨለማ ንግስ በአለም

በምድር ጠፋ ሰላም

መከራን በሶ በጽልመት ተደግፎ

ልምላሜ ከምድር ገጽ ደስታ ሰላም እንደ ቅጠል ረግፎ

ለጽልመት ቤት ሁሉ ተካቶ

ፍቅር ወደ መቃብር ተጎትቶ

በምትኩ ሞት ተተክቶ

ጨለማን ንጉስ ሆኖ ባለበት

ከምድር እውነት አጠፋሁት

ብርሃንን ከምድር ቀረብኩት

ምህረትን ከሲአል ጎተራ ከተኮትኩት

እውነትን የሰወረው

ተስፋን የቀበረው

የህያውን መንገድ የዘጋው

የቀዳሚት የጥፋት ሀውልት

ፈተና የተመለያበት

የስቃይና የዋይታ ሌሊት

ስደትና መከራ የተሸመበት

ኦዎ የሌሊት ነበር

በሰው በተፈጠረው የስርቆት ስር

የአዳም የተድላ ሀገር

የሄዋን የፍቅር የሰላም መንደር

በሰይጣን ሰፈር

በሀጢያት ተደራመሰ

በመብልገባ ከውድቀት

ሞት በሰፈሩ በሀረሩ ነገሰበት

የትልቅነት ተስፋ

የመኖር አደፈ

አራዊቱን ለመንዳት

የተሸመው በገነት ቤት

አዳም ነበር የተሰየመው ሰጥያዊ ክብር

እንዲገዛ ሁሉንም ፍጡር

ሲሻ አምላክ መሆን

ሁሉን አጥቶ መውደቅን

ተገነዘበ ከመከራ ሀገር ገብቶ

የአምላኩን  የፈረደባት ቃል ሰምቶ

ከመከራ ሀገር በጭንቅ በስቃይ

ይኖር ጀመር ስል እታች እሰማ

ጊዜያት ሄዱ እያለፉ

ወራት አመታት ከነፉ

የአዳም የተስፋ ቃል

እግዚአብሔር መጣ አክብሮውል

በአለም መሀከል

በቤተልሄም ክልለ

ተገኘ አመነዱ ብርሃን

ልያበራ ለአለምን

ዘራሽበት ትንብ ተናገረ

ስለ ብርሃን መውጣት መሰከረ

ከዘመናት በፊት ለልጆች ነገረ

ሄደው እንድያዘክሩ

ቤተልሄም እንዲዘምሩ

ትንብቱን አክብረው

በምልክቱ ተመርተው

የአይሁድን ንጉስ አገኙት

ከምድር ወድቀው ሰገዱለት

እጣን ከርቤ ወርቅ አመጡለት

ትህትናውን ተመለከቱት

ምን የምንድን ነው

ምን የሚገርም ነው

አዋፍን በክንፉ የሚያሸበርቅ

ምድርን በውበት የሚያደምቅ

አበቦች ቀለማት የምያሳብብ

ወድቆ ያየነው ከግርግርም

ለሰጠን ሰላም

በእመቤታችን በማርያም እቅፍ

ቤተልሄም ራደች

በፍርሃት ተንቀጠቀጠች

በሃሰት ዘለለች

በደስታ ተሞላች

በብርሃን ደመቀች

ተለያይተው የነበሩት ለዘመናት

ተራርቀው ለብዙ አመታት

ተገናኝተው ባንድነት

አምላካቸው አመሰገኑት

ያእቆብ ያየው መሰላል

ሰውና እግዚአብሔር ተሰብሮ ከመሃል

ተራርቀው ነበር

በዛሬው እለት

በዚህች አመሰኑት

ዳግም ተገናኑባት

አብረው በደስታ አከበሯት

በእልልታ አወደሷት

እረኞች ደረሳቸው ሰብከት

ሄደው ሲመለከተቱት

ሮጠው መጡ ከያሉበት

ወድቀው ሰገዱለት

የብርሃን መውጣት ተመለቱት

የጨለማውን ዘመን ረሱት

የጽመት ኑሮ ተውት

አለም ከጨለማ ተላቀቀች

ከሲኦል ተራጠቀች

የደስታ ብርሃን ፈነጠቀች

መድሃንአለም ተወለደ

ሴጣን ከምድር ተሰደደ

ለሌቱ ነጋ

የጨለማው በር ተዘጋ

ከተሾመ ኤጀረሳ

1989 ዓ.ም

# ነገሪ ስዲቶሽ

## በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

ያኔ ጥንት ድ አዳም ከገነት ተባሮ

ሲኖር ሳለ በዲያብሎስ ሸንገላ ተሳስሮ

የመዳን ተስፋ ሲያምረው

አዳም ጌታውን ስመነው

እግዚብሔር አምላክም ሰማው

ሀጢያቱንም ደቅሮ አለው

ከ 5500 ዘመን ሲፈጸም አድንሀለው

በሚል ቃል ደስታውን አበሰረው

ጌታም ቃሉን ጠብቆ መጣ

ከዳዊት ዘር ዘርን መርጦ

በድንግል ማህጸን ተቀምጦ

ሲያድነው ሲመጣ ፍቅር ሳለ

በድንግል ጹነስ የአዳም ልጅ ዳግም ተታለለ

ድንግል በድንጋኤ መጸነስዋን ባለማዋቅ

በአደሁድ ህግ ከለው ረቂቅ

ትወገር አሉ በመመጻደቅ

ሀቢቂዋ ዮሴፍም ተጠራጠረ

ተጨነቀ እጅግ ፈራ ተማረረ

ጌታ አምላክም ዝም አላለም

በመላው ቃል በራእይ በህልም አስመ

ዮሴፍ ዮሴፍ ብሎ ጠራው

ስለ ድንግል ጽንስ አበሰረው

ከመንፈስ ቅዱስ  በጽንስዋን ነገረው

አትፍራ አለው ወደ ቀጠራ እንዲሄድም አሳሰበው

ዮሴፍም በሙሉ እውነት እንዲሄድም አሳሰበው

ዩሴፍም በሙሉ እውነት ሳደጠራጠር

ደዞት ሄደ አብረው ሊቀጠረ

በዚያን ቀናት በዚያን ሰዓት

ሊቆጠር ጠላ የእስራኤል ህዝብ አያስበት

የሲየራሳሌም ህዝብ ተጠበበ

ህዝብ በህዝብ ሳይ ተደራረበ

ስቀጣፊው ባጠጣው ህዝብ ቤቶች ሁሉ ተጣበቡ

በዚያን እት ድንግል የምትወልድበት

ቦታ ጠፋ የአለም መድሀኒት

የአለም ጌታ ላለው ፍቅር ትህትና

በአብቶች በረት መወለድን መረጠና

ተወለደ የአለምን ህዝብ ሊያድናና

ያኔ ነበር የድንግል ስደት የጀመረው

ሄሮዶስ መንግስቴን ይወርሳል ብሎ ያሳደደው

አንዱን ልጁን ሲገድል ያሰበው

የአሸዋውን ግለት ስትመለከት

ያቺ ገጽ ህይወት ሳታታካት

ባለ አደራዬ ልጄ ተሰደደች

የግብጽን በረሃ በእግር አቋጠች

መራራ እንባ አነባች ስለ አለም መድሃኒት አለቀሰች

የክቡር ልጇን እንዳይገድልባት ፈራች

እሙ እመብርሃን ለኛ ብላ

መድኒአለምን አዝላ

መከራዋን ተቀደሰች በውሃጥም ተቃጥላ

ያቺ ብርሃን ርህርህተ

ቅድስት ቅዱሳን ባህሊተ ምህረት

ከጸሐይ ሀሩር ተቃጠለች

የብርሃንን ጸዳል እንዳቀረች

የኤልሻዳይ እናት የአለም መድሃኒት

የሰው ልጅ መደኛ የሆነች ክብርት

ፍቅረ ቅዱሳን እህተ መላእክት

ተቅዋመ ወርቅ የፈጣሪ እናት

ባለ አንድ ልጅ ስለ አለም አባት

ስቃዩ ተሰቃየች እሸህ ሁሉ ጠጋት

ስቃዩ በስቃዩ ላይ ተደራረበባት

ሀዘን በሀዘን ላይ ሰሉን አለበሳት

መከራው በጣም እጅጉን በዛባት

ቃጠሎውን ድንግል እንደምን ቻልሽው

የአንቺ አፈጣጠር የተለየ ነው

ለኛም ለልጆችሽ ድንግል ጸልዩልን

አምላክ እስራኤል ዙናት እንዲሰጠን

የሲዮብ ዙናትን እንዲያሰፋልን ::

ማስተዋል :- ሰላም ላንቺ ይሁን ቅድስት ኢትዩጲያ

የድያቆች አገር ሀይጠት መግቢያ

የህግና የፍትህ የአምላክ ቃል ማሰሚያ

አንቺ ነሽ በእውነት መጠጊያ

ሰጤንነት ሀይጠት ማጸበሪ

በአንቺ ቤት አለም የእውነት ገበያ

ኢትዮጲያ :- ፈጣሪ አምላክ ለኔ ለሰገሰው ሲሳይ

በአለም በመትረፍ በመሆኑ ከአፋ

ሁሉ ይጠይኛል በጣም ያፈቅረኛል

ደግ ናት ምረቃ ናት በጋስ ናት ደስኛል

ትዝብት የስንጀራ መገኛ ብትሆኝም ሀብታም

ወደድሽ ያልሆነ ጠላት አደቀምስውም

አበቦሽ የማደረግፍ አንቺ ነሽ ዘላለም

ሲትዮጲያ፡- አበር ደግባው ፈጣሪ ምስጋና ደድረሰው

ምንም ነገር የለው በኔ የጎለው

በሁሉ አስተካክሎ አሟልቶና ፈጥሮ

ውበትን ሰጥቶኛል እድልን ጨምሮ

ማስተዋል :- መልክ ደም ግብትሽ ቢያስኝም

ቁጭ ብድግ

ንጽህ አላላትሽ ጠበደሽ ሲባልግ

ባስመፈለጉ ስለሚኖር በህግ

ተደፍረሽ አታውቂም በአመንዝራዎች ጠግ

ሲትዮጲያ፡- ዝናቤን ያክሰማ አንዳንድ ቀጥቶ

የመልኬን ቁንጅና ደም ግባቱን አደቶ

ሲያረክሰኝ የሚሻ በአብሬት ተነሳስቶ

ወዲያው ደቀስፋል በአምላክ ፍርድ ተቀጥቶ

ትዝብት :- የኔ አስማት ፈጣሪን ሲት ቀን መስመኔ

በተንኮል ተመርተው አክፋ ያሰቢሽ

መቀሰም አያገኙ ጠፍፍሎ ጭራሽ

ኢትዮጲያ :- የኔ አለማት ፈጣሪን ሴት ቁን መስመኔ

ብልጽግናን መጥላቴ በህግ ማመኔ

ደህ ነው መስታ ድርቴ መታመኛ

ማስተዋል :- ሲያያዝ የመጣው ታፈክሽ መስክሯል

ልቅም ጥርት አድርጎ በማያወላውል

ከልጆችሽ በቀር የጭን አንገዳ

አለማስገባቱን በርሽ ሴላ በዳ

ተናርአል አጣርቶ በብዙ እያስፈዳ

ኢትዮጲያ:- ደሽንን የማያውቅ ያልተመፈመረ

አሸገር አየኝና ፈጥኖ እየበረረ

በመጣደፍ መጥቶ ለሲዩ ቢጠጣ

ጠዲያው ተገፍትሮ በጀርባው ተሰጣ

እሳት ለበለበው በጭፈሽ መቅና እጣ

አእር :-

እውነት ፈጣፈሽ ሀደሱ አምላክሽ

ጠብቆሽ ደኖፈል በክንፎቹ ጋርዶሽ

ስለዚህ አምላክሽ ለዋለው ውለታ

ብድረን መክፈያሽ መመለስ ጠርታ

በነቃ ህሊና ተግቶ መጸለይሽ

አዙን ነው አወቂያ መታዘዝ ለአምላክሽ

ማስተዋል

ስሚኝ ልብ ብለሽ እናት ኢትዮጲያ

ላፌ ፈተኛሽ ነው የሰንቺ መታጊያ

ብርታት ጥንካፌሽን ለዙሉም መሳፌያ

ላፌ ነው እወቂ ብርተው ያንቺን ትግል

ከአሳት ጋር ተላምደሽ እንዳትገቢ ገደል

አዙን ነው እወቂ መመርመር ማስተዋል

ላፌ ነው ላፌ ነው ጥንቃቄ ማድረግ

ካመዱ ገበር እርቀሽ ማስተዳደር በህግ

ላፌ ነው አዋቂ የሰንችን ስፉ መስፊያ

ልጆችሽን ሁሉ ወደ ህግ መምፊያ

ላፌ ነው ላፌ ነው ህዝብን ማስተዳደር

እንዳይለያዩም አስታቃቅፎ ማሰር

ላፌ ነው ላፌ ነው ህዝብን ማስተዳደር

አስምር

ቀዱሳን ምግባርሽም እንዳያረከብሽ

ከተንኮለኞች ምክር አጥብቀሽም መሸሽ

ላፌ ነው እወቂ ያቺን መጠበቂያልሽ

ከስልጣኔ ጋር ተዳብሎ የገባ

አለ መጥፎ ተግባር ስለ አንቺ የሚደረግ

ቅዱሳን ንጹሃን ለአንቺ የሚደረግ

በመርከብ ተጭኖ የመጣ ገብስብስ

አደጠቀምም አውቂ ደህ አደነት ልፈያ

በዚህ አደነት ተግባር ስለሰለቸን አሚሉሽ

መሻሉን አውቂ ድንቅር ናት ብለሽ

# ወስብሀት ለእግዚብሔር

# መች ወዳጅ አለና መልካም ቀን ሲከፋ

ሲመጣ በሰው ልጅ ምቀኝነት በአለም

ገቅ ብሎ እንጂ ክፍ ብሎ አይደለም

ይህን ይታወቅ ዘንድ ተንኮል ምቀኝነት

በአይሁድ በላይ አድረው ተባብረው በአንድነት

ከቀያፍ አደራሽ ተሰብስበው ሁሉ

ደለት መከራ ጌታን እንያዝ አሉ

ህውከት እንዳይመጣ ነገር ገን ህዝቡ

በበአል ቀን አይሁን አሉና ተግባቡ

ያን ጊዜም ይህ ከለሉ ፈጥኖ

በዚያች ቀን ተገኘ በራውም ታምኖ

በባለበት እጅ ድስት ሰሪ  ሆኖ

ከዚህም ቡሀላ መስሎ ልበቀና

ወደ ካህናቱ አለቆች ሄደና

እናንተ ምን ልትሰጠኝ ትችላላችሁ

ብሎ ጠየቃቸው መስሎ ባለ ጤና

አደሁድ ተስማምተው ደሁዳ እንደተገ

ሰላሳ ብር ቆርጠው የድካሙን ዋጋ

ወዲያውኑ ሰጡት ፍጹም እንዳደሰጋ

የአስቀሮቴ ደሁዳም ከዚያች ቀን ጀምሮ

ደኽ ጀመር ሰስቱት ስመቱን ጠንክር

ክፋት ገሸግስ ስደሁድን ሲመፈ

ጌታ ወደሰበት ፈቅ ካስ ስፍፈ

ጠደ ደረሰና ጌታንም ስገኘው

መምህር ሆደ ስንደት ዋልህ

ሲል ሰላምታ ሰጠው

ጌታም መለሰና ስምን መጣህ ቢለው

ደሁዳም ዝቅ ብሎ ጫማ እግረን ሳመው

ዛሬም ስንዳንድ ለው ወንድሙን ሲገዳ

በተገኘው ሰርስት ከዚህ ደሁዳ

ስንገቱን ደፍረው መለሱ ለሰው ትሀት

ቀና ብሎ ስደጣም ከገጽ ፊት ስፊት

በጌታችን መያዝ ሀዋርያት ፈርተው

መግቢያ መሸሸ ስሉ ሁሱም ተደጋገጠው

መች ወዳጅ ለስና መልካም ቀን ሲከፋ

የሰው ነዳነቱ ብርሃን ከጠፋ

ታውቀዋለህ ብለው ቢጠይቁት ከፋ

እሳት እየሞተ መለሱ ያንቀላፋ

በንታው መደብደብ ምንም ሳደከፍል

እባካችሁ ተውን እኔስ ስላውቀውም

ቢሉ አንገቱን ደፋ

በደስታ ጊዜ ነው ሲበሳ ሲመጣ

በክፋ ቀንማ መች ወዳጅ ሲመጣ

እግዚአብሔር አያድርስ አምሳክ አይቆጣ

በሀሙስ ሬት በግብዣው በልቆና ጠጥ

እኔ አለሁልህ በለው ስለ ነበር ተነስቶ

እጅግ ያለመጠን ሁሉም ተደስቶ

በበነጋታው ግን በክርሰቶስ በኩል

እጅግ እግር ታስሮ ሲመጣ ጦር መስቀል

ከ 12 ሰዎች በአል አቅመ መክቶ

በአርብ ቀን ጦርነት ከሰልፍ ሳይ ወጥቶ

ግዳጅ የሚፈጸም ሬት ለሬት ተዋግቶ

መከሬ ተካፋይ መጥ ዘመድ ተገኝ

በእርሱ ሳይ ጦር ሜዳ ሁሉም ተደናግጠው

መደበቂያ ሲሹ ሀዋርያት ፈርተው

ለሰው ልጅ መከሬ ሲመጣ ምን ጊዜም

ያ . . . . .ወልድ ነጓድጓድ አብሮ ከማርያም

የመስቀል ጦርነት በአይሁድም ሲፋፋም

ከጲሳጦስ አዳባባይ አስከ ቀሬንዮ ከገነቴ

መስቀል ሳይ ተሸክምህ ያዳም ዘር ሀጢያት

እንደ ሴሎች ፈርቶ ደንግጦ አልቆለም

በጌታ መስቀል ሰጠውን ያዘነች ወደዘር ጣደቱ

ወደዘርነ ጣደቱ ጥቁር ማቅ ለበሰች

ደረቷንም ጥላ ልብሷንም ባጭር ታጥቃ

ፊቷንም በእጇ እህቷም ጨረቃ

በተመለከተች ሁሉ በደም ተጥለቅልቃ

ነፍስም ስትለየው በ 5:00 ሰዓት

ሁሉት ሽማግሌዎች ከመስቀል አውርደው ውስደው ቀበረት

ጎታ እንዳደነሳ በመቃብር ጠባቶች

ምርጥ ጠታደሮች ከአደሁ ወገኖች

እንድን የታመቁት ተስዴተው ከሰው

ደጠብቁት ነበር ዙፊያውን ከበው

ክርስቶስ ሲነሳ ከተቀበረበት

መቃብሩን ከፍቶ በመንፈቀ ሌሊት

የድል ምልክቱን በቀኝ እጅ ነህ

ስልጣኑንም አሳደ እንደ ሀገግ ተመዞነ

ጠበቆች ወደቁ ለሁሉም ከያሉበት

ደንግጠዋልና በግርማ መልኩ

ተሬሮች ኮረብቶች ደስታን ገለጡ

በጣሙን ደነፋ የሆነቱን አጡ

ከመላእክት ጋርም ቤቶች ዘለሉ

ክርስቶስ ተንስአ እሙታን እያሉ

ከደቦታቸው ምበዛ ዘመሩ ጨፈሩ

የጌታን ትንሳኤ ለሁሉ አበሰረ

አሁን የት ይገኛል እንደዚህ ያለ ክብር

አስቀድ ማየት ከመላእክት ጋር የተንሳኡሉን ምስጢር

# መስብሃት ለእግዚብሔር

እርሷ ግን ነጎደች

ለእጇ ግን ሰላም ሳትጠኝ ተሰናበተች

ሩቅ ነውና ማደርያው

አዝና ተለየችኝ

ፈራ ብለ ለመሆን አውቃ ራቀችኝ

መልስ ለማግኘት ብዙ ግዜ ለምናኝ

ጥላኝ ሄደች ዳግም ሳታየኝ

ነገሩ እንዲህ ነበር

እግዚብሔር አገናኘችኝ ለቁ ነበር

እኔም በእርሷ እርሷ በአንድነት ልንበር

ፈጣኑን የፍቅ ባቡር

ተስፋርን ልንጓዝ አስከ ህይወት ትዳር

ማራኪ በሆነው ምክር

ሩህሩ በሆነ ንግግር

ሀጥያቴን ሸሽጋ ልትሰውር

የልቤን የሀጥያት ማህደር

ገልጦ ልትበረከር

ቀርባኝ ፈልቅቃ

ረጅሙን የሀጢያት እቃ

ጎትቼ ጎትቼ እንዳወጣ

የሩቅን ባህር ሀጢያት ጣልቃ

እርሷ ለአምላኳ የታመነች

በጸሎት የበረታች

በመልካም ምግባሯ የተካነች

በእውቀት ሳለ በመንፈስ የረካች

ረጋ ያለች አስተዋይ የሆነች

ከእነ ሀጥያቴ የወደደችኝ

ከውድቀቴ ገደል  ስታወጣኝ

ከማህበረ ክርስትያን ጨምረኝ

ቀረበችኝ

ከልቡናዬ የሀጥያት ባህር

በጥልቅ ቀድቼ ከእርሷ ሲነግር

ከእርሷ ጋር ህብረት ፈጥኜ ልኖር

ህይወቴን ለመቀየር

ጉዙፋኑን የሀጢያት ተራራ ለመናድ ስትጀምር

እኔ ግን ለስጋ ለመንፈሳዊ ህይወት ግድ አልነበረኝም ከዚህ ይልቅ ለስጋ ለሽቀረቀር

ዘካሪና መከራዬ

እህቴበ አሳብዬ

እንድህ እያለች ልቤን ስትሰብር

ልታሰራኝ ቁብ ነበር

ህያው ነህ ጓዴ የምወድህ

ሀጢያት በዝታ እንዳትወስድህ

የሀጥያት ወንዙ ሰፊስ ጎትቶ

ቡሀላ ስመጣ ጌታ

የማታ ማታ ድል የሚመታ

በመንግስቱ ለዘላለም አለህ ቦታ

እያለች በማራኪ አንደበት

በታመመ መንፈሳዊ ህይወት

በጥበብና በብልሃት

ደጋግማ ያለመሰልቸት

መከራችኝ ዘከረችኝ

መጽሐፍ ቅዱስ ገዝታ

መንፈሳዊ ህይወት የሚጠቅመኝን አምኜታ

ሁል ግዜ ተገኝታ

ህይወቴን ከጥፋት ልትታደግ

ስለ አምላክ ፍቅር ሁሉን ልታደርግ

እኔ ቤተ ክርስቲያን ሁሉን ልታደርግ

በሀጥያቱ ከመርኩስ

ከመጥፎ ህይወት ለመመለስ

አንዳች አቅም አጥቼ

በሱስና በስንፍና ታግቼ

ለ አራት አመት ከእርሷ ጋር ቆየሁ

ለእኔ የነበራት ፍቅር አየሁ

አሳቶችኝ ብዙ ገዳማትን አዙረኝ

እለውጥ እንደሆን ብላኝ

ገን እኔ የማልጠቅም ባርያ

ዳግም ወደ ቀድሞ ገብሬ እንደ ተመለሰች ወደ አመድ አህያ

ስለ እኔ አዘነች

ሱባኤ ገባች ያመች ጸለየች

እኔን ከሀጥያት ለመመለስ ጌታ ያደረገውን መከራርን ስቃዩን

እያዋለች ዛሬም በሀጢያት እርም እንድል

ለጋን ለማሸነፍ እንድጀምር ትግል

ነገም መግብያ ስለ ኢየሩሳሌም ሀገሬ

ውጤቱ ሰምሮ እንዳፈራ ፍሬ

ይቅር መበደል ከጉህ በላይ

ይታወስህ የቀራንዬ የአምላክ ስቃይ

እነርሱ የታመመ ህመምተኛ

ለእኛ ስርየት ሀጥያት አይደለም

ምክሬን ለምንድነው ያልከው ዝም

ነገ አንተ አትሞትም

ድምጻን አድምኛ ሀጥያት ተው በይፋ

ነገን እንድኖር በፈላች ተስፋ

ብዙ ስላለኝ ብዙ መከራ

ለሰው ነግሬ ዝክራ

ጸሎት አድርጋ ሴባኤ ገብታ ነበር

እኔን በሀጥያት ወደ ጽድቅ ለማሻገር

እኔን በትመልስ ብዙ ጣረች

ህይወቱ በስዝር አልታጠፈች

በምግባሬ አዝና አለምን ጠላች

በዚህ ህይወት መቀጠሌ

እንዳታይ ውዳ አካሬ

ቤተሰቧን ዘመደቻን ጥላ ጠፋች

ዳግመኛ ላገኛት ብሎ

ዘሬ ቢፈልግም

አብያተ ቤተ ክርስቲያን ተሳለምኩ

ትገባለች ባልኩት ቦታ ዋልኩ

ሁለት አመት አለፈ

ብዙውን የንስሃ ዘመኔ በከንቱ አከፈ

እንዳላገኛት አውቃ ዳግመኛ ወደ ሀጥያት ተመልሽ

ገፋፈሁባት ሀጥያቴንም አታራምሽ

ወዴ ሀገር ነው ኢየሩሳሌም

አይደለች አለም

ሀጥያት አታሰገኝም ሰላም

ከእኔ ሀገር እንድትሆን ሁሌም

እያለ ጭቅንቅሏቷን ሰያጭቅል

የሀጢያት ገደል

ከመነሳበን ባለው ይመጣል

ወደ ሀጥያት አለም ሲሄዱ

ረቂቅ መሀላቸውን ያለው መንገድ

ጊዜው አርቆ ሰገፉ

ሰጠፉ ተስፉ

እኔ በጨለማው አለም ስኳትን

አስደስቼ ዲያብሎስን

ግን አንድ ቀን ልንገስ ከአንድ ታላቅ ገምዴ ሄጃ

ከመቅደሱ ደርሼ ሰግጀ

በምእመኑ ቤዛት ገዳ ሲታጨቅ

በምስጋና በዝማሬ ሰትደምቅ

ሰው አይነት

ሽማግሌ ህጻናት

የበአሉ ድምቀት

ልቤ ተነክቶ ለጸሎት

ገባሁ ዉሰኛ ከቤተ መቅደስ

ገብቼ ሰስግድ ስነሳ ስወድቅ

የበደሌን ታሪክ በምጥብሳውሳ

ደክሞኝ ሲቀመጥ

ከቤተ መቅደስ አይኔ ሲቀላውኝ

አንዲት ወጣት መነኩሴ ጀርባው የሚታየኝ

እየወደቀች እየተነሳች ስትሰግድ ጥንካሬዋን አዳናብኝ

አይኔን ሳልነቅል

ስግደቱን ስታበቃ ተሱ ሰትል

መብረቅ እንደመታኝ

ደርቄ ከተቀመጥኩት ቀረሁኝ

ልቡናዬ ስመታ

አይኔ አርሷን እያየ ሲንገላታ

ያቺ መነሰኩሴ ከጓደኟቿ ጋር መሀል፣

ሄዳ ሰትቀመጥ እኔ አላቋር እርሷን ያየለ

ደንገት ሳላስበው

ፍቱን እንባ ሞላው

ህልናዬን ኮርክሮ

የልብን መዘገብ ቦርብሮ

ሲፈትሽ ታሪኬን

ውሏቷ መነኩሴ እማሆይን

በአሉ ሲያበቃ ተነስቼ

እቃዬን ሻንጣዬ

ተደብቄ ተሰውሬ ጉዙ ልጀምር

የዚያች ወጣት መነኩሴ ነገው

ለህልናዬ እረፍት ነስቶኝ ስቸገር

ድንገት ከኋላዬ ዜማ በማስመሰል ቃል

የዮፍታዬ የሚል ቃል ሲያቃልል

ከሃሳብ ማእበል ሰነቃ ዞር ብዬ ሳበቃ

ያች የመከረችኝ የዘከረችኝ

ስለ ሀጥያቴ የተሰቃየች የታመመች

ምህረት ነበረች

ፈጥኜ ከእግጃ ሰው ወድቄ አለቀስኩኝ

ይቅር ይለኝ ብሎ ተማጸንኝ

እርሷ ቃል አልነበራትም

የምታወራልኝ የሚትራኝ በእውነትም

እንባዋ ጠብ ጠብ ሳል

ተያይዘን ስንላቀስ ብዙ ትግል

ሁለቱ ጓደኞቼ አለቀውን

አንደበቱ ታስሮ ሰጠቀኝ የምለውን

ከብዙ ለቅሶ ቡኋላ

የዬፍትሄ ተለውጦህ ንስሃ ገብተሃል

ብትለኝ ከቶ

አንደበቱ መልስ አጥቶ

እየተንቀጠቀጥኩኝ በሀጥያት መኖሬን

እስከ ዛሬ እየበደልኩ እንደሆን

ሲነግራት

ምንም ቃል መጣት

እያለቀሰች በእንባ ተሳነበተች

ደግሜ ብጠራት

መልሷ ለቅሶ ነበር

ምክንያት ደርድሬ እርቅ እንዳገኝ

እርሷ ከጓደኞቼ ከትልቅ ካቻማሊ ገብተው

ቃል ሳይነግሩኝ እርሷን ጎትተው

ከመኪና ገብተው ስሄዱ

እየራቁ ሄደው ሀጥያት አመለሰ

ብዬ እርሷን ልዶስ

የምህረትን እንባ ስላለ

ይኸው ተነስቻለሀው

ወደ ሱባኤው በንስሃው ለመድረስ ልገስግሰው

ቀን ለጎደለበት ቆሽትን አማረረ

ከሰው ጋር ግን ሆና ሁል ጊዜ ጠፋሪ

የኔ ቢጤ ድሃ የቁም ነገር ምናን ሲያጥም

ምራቅ እህል ሆኖት ባፏ ውስጥና ሲያምጭና

መች ደረሰችለት መች እራራለችለት

ደስ ብሏት ጭራሽ ቢሉ እየተሳለቀች

ሰው ገድልህም ቢሆን ሰርቀህ አምጣ እያለች

ሀብታም እንደደሚሆን ተስፋ እየመገበች

ኧረ ስንቱን ስንቱን ነው ያጠፋች

የሰውን አላውቅም ልንገራችሁ በእውነት

ይህን ትመስላለች አለም እንዳይጎት

እያናቅራቸው አንዱን ባንዱ ጋር

ባልም ሰይጣን በሷ አባውራ

ጠፋውን በሚያዛት ሁሉን በየተራ

ኖረች ሁል ጊዜ አሁንም አለችው

ጤች ይሆን ጊዜያቱ የሷን መጥፊያ የማዳሙ

እባክህ ክርስቶስ ቶሎ በል መጥተህልን

አንቺን ----------በደመሰስክልኝ

መች የሷ ታሪክ እንዲህ በቀላል

ተዘርዝሮ ያልቃል ታጽፎ በቀላሉ

እንደው ለነገሩ ልጣራው በብእሬ

ያየሁትን ጉዷን ለአለም ወሬ

ሀዘን ጎኑን ወጣት ድሀው የትም ሲወድቅ

ዋልታና ምሶሶው  በላይ ላይ ሲናድ በእጦት ሲመጣለቅ

አለም እሺ እንዲህ ናት ሰው ሲበጫን የምታስቅ

አምላክ ፈጣሪ  ለሰው ልጅ መፈንጫ

እሷ ግን ስትሆን ከሀዲ ሞላጫ

በይኔ አይቻል ደርሶኛል በኔም

ለሰው ዘር ቢጣሉ ፈጽሞ አትመችም

የሀዘን ማቅ ሲወርስ ህይወቱ ሲዛባ

ጸሀው ቅጥ ሲያልቅ ቁጭ ብሎ ሲያነሳ

ዳልሙ ጋር ትደርቅ ስትል ኑሮራወሸባ

ደጣሮ ጭቅ ሲያልቅ ቁጭ ብሎ ሲያነባ

ዳግም ገንዘቡ ሲያልቅ ሂድ ከዚህ ስትለው

አቤት የሷም ነገር ላለው አትሆነው

ችግር ረሀብ አንገቱን ሲያስደፋው

ከገጠቡ ሆና መች አለሁ አለችው

አቤት ስለ አለም ምን ብዬ ልናገር

በምን ቃል ተጽፎ በጭን ድምጽ ይነገር

እስቲ ጥያቄ አለኝ ልጠይቅ በኔ አፍ

ወረተኝነት በምን ቋንቋ ልጻፍ

በማረኝ እንዳልል ፊደላቱ ሁሉ

የሷን መጥፎነቷን ብዙም አያጎለለ

በእንግዚዘኛ ላርገው ምናልባት ሲሻለኝ

እሱም ችግር አለው ትርጉሙን አላገኝ

እስቲ ለምን ልጻፍ --------ንገሩኝ

እንደው ብቻ ስሙኝ እውነት ልንገራችሁ

የጭቃ ሙስና እሾህ የምትሆን ሆነባችሁ

በጦር አስዋወሳ መርዝ የምትሰጣችሁ

በድፍረት መሰንክሩ አለም ናት ብላችሁ

አዳነው በይናችን ለኛ ተሰጠን

የሰው ልጅ ሲታመስ በላም ውስና ሲባዝን

ለማንም የማትሆን የጨለማ ውስጥ ምጥ

ጉልበቱን አጣጥፎ ካንጀቱ አሰጣጠት

የኔ ቢጫው ድሀው የሚያዘግየው እናት

መች ደረሰችለት ሲኖር ተንላት

እያየች  ሲገነዝ የቁም ሞትን ሞት

የሰውን አላውቅም ልንገራቸው በእውነት

ይህን ትመስላለች አለም እንዲያየአት

በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት በጻድቃን ሰማእታት ተረዳኢነት እያመንኩና እየተማጸንኩ ይህችን መላእክት ለኪነ ጥበብ አዘጋጆች ስልክ በጣም ተደስቻለሁ በርታ እግዚአብሔርም ይርዳችሁ የአምላክ እናት ትምራችሁ መላእክት ከክፉ ነገር ይጠብቋችሁ እያልኩ ውድ የኪነ ጥበብ አዘጋጆች ለዝግጅታችሁ ለመሳተፍ ያህል ይህችን ስነ ግጥም ልኬላችኋለሁ እንደምትሆን አድርጓት

“ በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም አጋንንትም ለማስወጣት ከእግዚአብሔር ሀይል ለማግኘት ጾም አስፈላጊ መሆኑን ጌታ ተነግሯል ማርቆስ 9-29

ቃል ኪዳን ገብተናል

የተፈጥሮ ህግጋቱ

ሳይዛባ በሂደቱ

ቅደም ተከተል ጠብቅ

ለዚህ ቀርቦ ከዚያ ርቆ

የነበረውን አጥፍቶ

ያልነበረውን ተክቶ

ትልልቁን አሳንሶ ፣አደህይቶ ታቻ አድርሶ

ተራ ሰጥቶ አኗለኛው

ከሱ በላይ እንዲያኖረው

እኛም አይተን የጊዜን ህግ

አድንቀናል ምን እናድርግ

አየህ ነበር የሰው ባህል

ሲናገራት እንዴት ይቀል

አንቺም እኮ በሂደቱ

እልፊሽ ነበር በጥዋቱ

ስም አይጠፋም ሌላው ቢቀር

ህያው ታሪክ አይቀበር

አይረሳም በዘመናት

ስምሽ ያው ነው መዝገበ ምህረት

እኛም አንቺን ላንረሳ

ያንቺን ታሪክ ልናወሳ

ድንግል ማርያምን ተማምነን

ለኛ ብለን እንደክማለን

ሁሉም አለ እሱ ካለ

አለ እሰማ ምንስ አለ

ላንክድሽ እናታችን

ቃል ገብተናል አንድ ሁነን

ብንርቅም ልጆችሽ ነን

ብንርቅም ልጆችሽ ነን

ወስብሀት ለእግዚአብሔር

በኪነ ጥበብ ----------አዘጋጆች

# አደራ እልሻለሁ

በዚያ በበረሃ ምንም በሌለበት

ተሰደሽ የኖርሽው ሳይኖርብሽ ሀጢአት

የሰው ልጆች ቤዛ የመኮት እናት

ቅድስት እናታችን የዋኋ እመቤት

አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ

ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያላንቺ ጠባቂ

አድኝኝ እናቴ ከስጋ  ከፈተና

እኔማ ያንቺ አልችልም ልጸና

ቅድስት ሆይ አትራቂኝ አንቺ የአለም እናት

በዝቷል መከራዬ አድኝኝ ከጥፋት

ሸክሜ የከበደኝ እንግልት ሆኖለሁ

ከኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ

**ምንጭ ሐመር ሁለተኛው አመት ቁጥር 4 ጥር 1987 ዓ.ም)**

ኧረ ማን ነው

የበደለውን አስታውሶ

ያጠፋውን ክሶ

ያለውን ለግሶ

ታዛዥ ለፈጣሪ

እውነትን መስካሪ

የእምትን ፋና አብሪ

ማነው እውነተኛ

ከሀጢአት ጸሞኛ

የእግዜር ግጥም

ፊደል ተገጣጥሞ በአንድ ተጠቅልሎ

ስሜትን በመንካት ቤት ደፍቷል ተብሎ

ስያሜን ተችሮት የመግቢያ መግለጫ

ለእያንዳንዱ ሀሳብ ሰጥቶ ማስረገጫ

የልባችን ስሜት በቀለም ሲወጡ

ተብሎ ይነበባል ግጥሙን ገጠመው

የእግዜር ግን -------የእግዜር ግን ልዩ ነው ግጥሙ

መስማት የማይችሉት ከባድ ነው ሽክሙ

የኔም ------የኔም ግጥም እርሱ ነው

እጆቹን ዘርግቶ በመስቀሉ ያለው

የጻፍኩትን ሀሳብ ለአእምሮዬ የሳለው

አዎን . . . .አዎን ግጥም እርሱ ነው የሀሳቤ አፍላቂ

ለምስለው ስእል ቀለሜን አርቃቂ

ስለ እርሱ ግጥም ልበል እስቲ በግጥሜ

የጻፍኩት የሳልሱት እስኪል አቅሜ

ፍጥረትን ሲያበጃጅ በፈጣሪነት

ከስራቸው ስራ ከስነ ፍጥረቱ

የእናንተን አላውቅም የእኔን ግን ልመስክር

ያየሁትን ነበር ሆኜ ከመስቀል ስር

ጌታዬ ------አዎን ጌታዬ ጎበዝ ገጣሚ ነው

ምስጢሩን ትርጉሙን ማንም የማያውቀው

በጠቃሚነቱን አይን አስፈለገና

አፍና አፍንጫ እነርሱም ታዩና

ይጠቅማሉ ተብለው በፊት ላይ ከተሙ

ባፈር ቀለምነት በእግዜር ተገጠሙ

ይሰይበት ዘንድ እጅም ተረቀቀ

እንዝበት ሲባል እግርም ተዋቀረ

እነዚህን ሁሉ ገጥሞ ጨረሰና

ያስተውሉ ብሎ ሰጣቸው ልቦና

ከዳዊት ጋረደው

ዘቂርቆስ ወልደ ብርሃን

ለእኔ ያርገው እንዳልልህ

ቀርጥ አንተ ሆኜ በአርያህ ፈጥረኸኝ

ጸምግባት ውበትን ቁመና ሰጥተኸኝ

በስሜም በግብሬም አንተን እየነገርኩ

ያሻኝን በሙሉ በሰጠኸኝ ስልጣን

ሳልዝል እየፈጸምኩ

ሳወጣም ከገባም አይኖችህን እያዩኝ

ከውድቅ አንስተህ ኸረ እስከ መውደቅ ስትሰጠኝ

በአባትህ ፍቅርህ ልጅ ምትለኝ

ለአንተ ለአባቱ ዛሬ ውለታ ቢስ ሆኜ

መከራህን ተመልክቼ እንዳላየሁ አይኖቼን ሸፍኜ

ወዜን በግንባሬ እንደ ውሃ ምንጭ ያፈለከው

ቁንጅናህን በስቃይህ እየነሱህ ባየው

ለእኔ ያ ርገው እንዳልለህ

መመታትህ መጨፍጨፍህ

በሚስማር መቸንክርህ

በመስቀልም መሰቀልህም

ውርደቱንም ቢሆን ክብር ማጣቱንም

ለእኔ ያረገው እንዳልልህ ጌታ ሆይ አልችልም

ከዳዊት ጋርደው

24/07/2001 ዓ.ም

ሌባ ላመሉ

ሌላ ላመሉ ብለው የተረቱት

የሌባን ምንነት በቅኔ ያስቀመጡት

ፍዳውን አይተው ነውና ዳቦ ይልካል ያሉት

አሰይዞታልና አለቃውን ስሞት

ልመና

የአዳምን ጸጋ ሰጠኝ አልልህም

ዳግሞም እንደ አቤል አርገኝ ብዬ ፍጹም አለምንም

የቃልንም ቢሆን ነፍስ ገዳይነቱንም ፈጽሞ አልመኝም

ማቱሳላን ልምሰል ብዬ አልጠይቅም ከቶ

አብርሐምንም ልሁን አልል ዛሬ ካ ሸዋ ይልቅ በዝቶ

አልሞትም አልልም ሄኖክ ስላልሞተ

እንደ ልብህ ልሁን ብዬ አልለምንም እንደ አባቱ ዳዊት አንተን እንዳስደስት

ልጠይቅም አልሻም ልሁን ብዬ ከሰው ልብ

እነዚህን ሁሉ አልልህም ሰጠኝ

እኔ ምለምንህ አንዲ ጸሎት አለኝ

መንግስትህን ስትመጣ አደራ አስበኝ

ገጣሚ ዳዊት ጋረደው

አቅራቢ ፡- ፍቀረ ዮሐንስ ሰማ

**በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን**

አንተ ባለህበት

ምንም በደል ቢኖር

ሀጢአትም ቢበዛ

የመታዘዝ ፍሬ

ከሰዎች ቢታጣ

የፅድቅ ስራ ጠፍቶ

አመጽ ቢበረታ

አንተ ባለህበት -----

በዚያ ምህረት አለ

ከነኔም የለበት

የሚያስደንቅ ማዳን

ፍቅር የሞላበት

የይቅርታ ጉዞ

ጽድቅ የሰፈነበት

----ምን ጠላት ቢበዛ

ሀይሉም ቢበረታ

ቀንበሩም ቢጸና

ቢበዛም ሁካታ

አስፈሪ ነበልባል

እጅግ ቢንበለበል

ውሀውም ቢፈላ

ቢፍለቀለቅ በሀይል

የኤርትራ ባህር

በሰፊው ቢንጣለል

ወደ አንበሶች ጉድጓድ መጣል

አንተ ባለህበት

ጠላት ያሸንፋል

የእብሪቱ ድልድይ

በቃልህ ይናዳል

ነጻነት ታውጆ

ቀንበሩም ይነሳል

ፍል ውሃው ቀዝቅዞ

እሳቱም ይጠፋል

ባህሩ እንደተራራ

ቀጥ ብሎ ይቆማል

ጠላት ከነጀሌው

በውሃ ይበላል

ውሃ ውስጥ ይሰጥማል

የአናብስቱም አፍ

በሀይልህ ይዘጋል

----ነውጡ እጅግ ቢያይል

ማእበል ቢነሳ

ተስፋ መቁረጥ ነግሶ

ቢበዛም አበሳ

**መቅደስ አያሌው**

**ከደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን**

# መዝሙር አለቀሰ

የያሬድ ዝማሬ ፣ የአዘማማር ስልቱ

የበገናው ቃና ፣ የማሲንቆው ቅኝቱ

የከበሮው ውበት የዋሽንት ፍሰቱ መዝሙር አለቀሰ ተገፍቶ መብቱ

ነበር ተፈጥሯቸው ስብሀት ሲዘሩ ተጥሶ ስርአቱ

ሰርአት ሊያከብሩ ዲ/ን አበበ ጥላሁን

መንፈስን አድሰው ውበት ሊደምሩ ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ

ምህላ ሊያደርሱ ኑዛዜ ሊያወሩ ክረም ግቢ ጉባኤ

ስንድዋ እመቤት ቤተ ክርስቲያን ቅድስት

እንዳላስተማረች ሁሉን በስርአት

ዛሬማ አፍ የፈታ ሁሉ እያንጎራጎረ

ቀኖና ትውፊቱን እየሸረሸረ

መዝሙር ዜማ ሳይሆን ጩኸት ሆኖ ቀረ

ለነፍስ ሀሴት ትቶ ለስጋ አደረ

ሲኦልም ከደዌው እንዳልተፈወሰ

ወኂኒውም በመዝሙር እንዳልፈራረሰ

መዝሙር ቅዱሳንን እንዳላወደሰ

ዜማን ሀዘን ገባው መዝሙር አለቀሰ

ንጉስ ገብረ መስቀል ጦር ከእግሩ ሰክቶ

በፍጹም ተመስጦ አለምን ረስቶ

እንዳልነበር ሁሉ ጸጋችን ምግባችን

መዝሙር አንገት ከመላእክት በላይ አዋቂዎች ሆነን

ሳይጠፋ መዝሙሩ እስከ ስርአቱ

ፈር እየቀቀ ዘማሪ ነኝ አለ ሁሉም በየቤቱ

በጠፋበት ሁሉ ተሰጥኦው መክሊቱ

ምንድን ነው ምስጢሩ

ያልተማሩ ናቸው አባትና እናቱ

ግን ይገዙ ነበር ለፈጣሪ አባቱ

ምንም ባይማሩ ባይመራመሩ

ፈርሀ - እግዜር ያላቸው ጥሩ ሰው ነበሩ

የዛሬዎቹ ግን ተማርን የሚሉት የተመራመሩ

በምድር ቢኝዙ በሰማይ ቢበሩ

በስጋቸው ብቻ ሁል ግዜ አጣሩ

ምስኪንን ካልረዱ እግዜርን ካልፈሩ

የእነርሱ መማር ምንድን ነው ምስጢሩ

የት ነው ቁም ነገሩ

በመሬት ላይ ኖረው

ለካስ ከንቱ ኖሯል

ሰውን አየሁ ቀጥ ሲሄድ በእግሩ

ነገ ተጨልዬ ሊገባ ሻፈሩ

አምሮበት በስጋ ምርጡን ሁሉ ለብሶ

ነገ ከታች ሊመጣ ድንጋይ ተንተርሶ

ምኑንም ሳያስብ ስለሰነፍ ጣጣ

በአለማዋዊ ኑሮ ሲኒር ሲቀናጣ

እያስታውሉ ሁሉም ዛሬን ብቻ እያለ

የሰው ልጅ በክንቱ ቀሪ እያጣለለ

ነፍስ ባህሪዋ አምላኳን ስትሻ

በስጋ ገበያ ሳታጣ መድረሻ

እባክህን እያለች እየለመነች

ስጋ እያባበለች ነፍስን በደለችው

ለካስ ሽንቱ ኖሯል የሰው ልጅ -----

ነፍስን ቢበድል ለስጋ መድከሙ

በስጋ ታሸብርቅ ነፍስ መች በቁጣት

እፏኝ ስንቅ ለመንገድ ለጉዞም አልሆናት

መልባችን ሁሉ ቆን መሄዳችን

ነፍስ ካለችበት በመልካም ስራችን

ለካስ ክንቱ ኖሯል አለን ጠላታችን

**ምንጭ ከመለኮት**

**ዋሲሁን ቁጥር 10**

**ወስብሃት ለእግዚአብሔር**

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

# አንተ ባለህበት

ይታዘዛል ባህሩ
ነውጡም ሀይሉን
ጽጥ ይላል ማእበሉ
---አሳዎች በባህር
አንዳችም ባይኖሩ
መረቡም ባይሞላ
ድካም ቢሆን ትርፉ
አንተ ባለህበት
ማጣት የለም ከቶ
ረሃብ ይወገዳል
አሳው ተትረፍርፎ
መረቡም ሞልቶ
---ህመም ደዌ ጸንቶ
ህይወት ብትደበዝዝ
አስታማሚ ጠፍቶ
ባይኖርም የሚያግዝ
አንተ ባለህበት------
መድሃኒት መች ጠፍቶ
የማያየው ሁሉ
ይመለሳል አይቶ
በደስታ ይቦርቃል
ለምጻሙ ሰው ነጽቶ
ዲዳው ይናገራል
ይጮሃል አብዝቶ

ምን ሞት ቢበረታ
ቢያይል ፍርሃቱ
ብቸኝነት ነግሶ
ቢበዛ ጭንቀቱ
አንተ ባለህበት -----
ሞት ስልጣኑን ያጣል
ማንቀላፋት የለም
የሞተም ይነሳል
ሀዘኑ በደስታ
ሞትም በትንሳኤ
በአንተ ይለወጣል
ስለዚህ ጌታ ሆይ
በአንተ ሁሉ ካለ
የአንተ ልሁንና
ሁሉን ግኝ ከአንተ

**ወስብሃት ለእግዚአብሔር**

ሁለተኛው ሽፍታ ትእዛዙንም ተቀብሎ ጉራዴውን መዘዘው

በዚህን ግዜ ምን ይዋጥሽ

ከፍተኛ ተማረርሽ እምረርሽም አለቀወሰሽ

ምን ታደርጊያው አንድ ልጅሽ

የምታይው እንደ አይን ብሌንሽ

አይንሽ እያዩ ሊገድሉት ነውና

እረ ስለ እግዚብሔር ስትያቸው ገና

ማን ይስማሽ ልባቸው እንደ ብረት የደነደነ ነውና

አለ አንደተኛው ከፍታ ከግራሩ ደንድ አስደገፈው ቶሎ

አንደኛው ከፍታ መጣና በቶሎ

ከጉያሽ መንጭቆ ሊነጥቅሽ ጠጋ ብሎ

ታድያ ተደግፈው የነበረው ትልቁ ግራር

ሁሉት ቦታ ተቀፍሎ እንደ ሸተር

እውስጥ ገብታችሁ ስትወሩ

ከፍተኛ በጣም ደነገጠ ባለሆነባቸው ውድያው በረሩ

ድንግል ምን ስሜት ተሰማሽ

ምንስ አልሽ በእውንሽ

ምን ተሰማሽ ስለመወደድሽ

እስቲ ንገሪኝ እባክሽ

10/02/1990 ዓ.ም

እ.ር

ኪዳነ ገ/መድህን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# ምንድን ነው ምስጢሩ

ያልተማሩ ናቸው አባትና እናቴ

ግን ይገዙ ነበር ለፈጣሪ አባትዬ

ምንም ባይማሩ ባይመረመሩ

ፈረሃ እግዜር አላቸው ጥሩ ሰው ነበሩ

የዛሬዎቹ ግን ተማርን የሚሉት የተመራመሩ

በምድር ቢጓዙ በሰማይ ቢበሩ

ለስጋቸው ብቻ ሁል ጊዜ ከጣሩ

ሚስኪንን ካልረዱ እግዜርን ካልፈሩ

የእነርሱ መማር ምንድን ነው ምስጥሩ

የት ነው ቁም ነገሩ

ወገን ካልጠቀሙ ለሀገር ካልሰሩ

ነፍሳቸውን ትተው በስጋ ከአደሩ

በስጋቸው ምቾት አለምን ቢዞሩ

ማስተማር ዶክተር የሚል ማእረግ

ቢከምሩ

መች ገባ ሚስጥሩ

ህጉን ተማሩ

እግዜርን ካልፈሩ

ተሸሉ የለምድ እኒያ ያልተማሩ

በህገ ልቦና ታቅበው የኖሩ

በወዛቸው ውጤት የሚተዳደሩ

ያላጭበረበሩ

ያላመነዙረ

እግዜርን የሚፈሩ

# ገናነህ ደስኪል

ነገሩ አልገባኝም የወንድሜ አባባል

ሁልጊዜ ሊያገኝኝ ገናነህ ይለኛል

በእውነት ገና ነኝ

ከየት ነው የምተመጣው ብሎጤቀኝ

ከቤቱ በተክርስቲያን ብ እኔም መለስኩለት፣

አንተ ቂስ አይደለህ እልያም ዲያቆን

ሁሌ የምትሁድ ቤተ ክርስትያን

ይልቅ አትጃጃል ዛሬ እንጫጫሽ

ኦላ እንዳይቆም ወደኛ ተመለስ

እንብላ እንጠጣ በላን እንዝናና

ይህ ዕድሜ አልፎ ይቆጭሃልና

ሃጥያት እኮ ነው

ሄዲያ ሓጢያት ዕድቅ አትበለኝ

ምንም አትንገረኝ

ሁሉኑም አውቃለው መጨ እኔ ጠፋኝ

አሁን አይደል ጊዜው መሄድ ቤተክርስቲያን

አለው ጊዜ ስንጠግብ እድሜን

አንተማ ተቀበለኝ ከንቱ አትንጦልጠል

ቤተ ክርስቲያን ልትሄድ ገና ይቀርሃል

በእውነት ገና ነኝ

ይገርምሃል ወንድሜ ባገኘኝ ቁጥር

ይናገረኛል ሁሌ የጥፋት ምክር

በጉብዝና ወራት ፈጣሪህን ሃስብ

ለዚህ ነው ማለት እንዳይመጣ ሰበብ

ቤተክርስቲያን መሄድ ክልሆነብኝ ካህን

አትሂድ ያለው ኧረ ማን ይሆን

ደግሞስ በእርምጃ እሄዳለው ያለኝ

ማርጀቱን መች አውቆት እንደዚህ ሚለኝ

እንኳን የአመቱን ያሁኑን አናውቅም

ተዘጋጅቶ መኖር ነውና ሚጠቅም

ማጨስስ ለምኔ ለማንስ በጅቶ

እናጭሳ አለኛ አፉን መልቶ

ዘና ያደረገዋል ማጨስ ማቀሙ

ደብድብ ይመስለዋል ለእርሱ መስከሩ ነው

ትላንት እንደ ጉድ ተቃመ እንደ ጉድ ተጠጣ

ይለኛል ሲያገናኝ ካለበት ሲመጣ **“ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወላዲተ ድንግል ወለመስቀሉ ክብሩ**

በኖህ ዘመን ያሉት ንስሀ ሳይገቡ መጨፈር አምሯቸው

በሃያ እንጋባለን መቶ እንጨፍር እያሉ ሲዘሉ ጠፉ ከምድር

አቤቱ አምላኬ እኔን ልጅህን በቤትህ ውስጥ አጽናኝ ልተግብር ቃልህን

ይህን ወንድሜንም ማዳኑ አቅርቦ ካለም ውስጥ ይውጣ ወደ ቤትህ ጥራው

ይገርማል በእውነት ገና ነኝ

ዘወተር አሁን እንጨፍር ሲመጣ እርጅና እንሄዳለደን አብረን መቼ እንቀርና

ሁልጊዜ ሲያገኘኝ ነገሩ ገርሞኛል

የወንድሜ አባባል ቤተክርስቲያን ሲሄድ ገና ነህ ይለኛል

በእውነት ገና ነኝ

እሱም ምንም ቢለኝ አምላኬ ጠርቶኛል

ትእዛዝ ያከብሩ

የዱሮዎች አባት የዱሮዎች እናት

ደግ ሰው ነበሩ

የዋኖችን ታሪክ ትውልድ እንውረሰው

በእኔ አቅም ተገልጻአ  መቼም አልጨርሰው

ነገሬን በስጥር

እንደ አባት አብርሃም እንሁን ደግ ሰው

አምላክ አለምን በፍቅ አዳነው

ስጋውን ቆርሰው

ደሙን አፈሰሰው

ትውልድ እንድትርሰው

ዘላላም አስታውሰው

ዘወትር ቅመሸው

ዘላለም አስታውሰው

ዘወትር ቅመሰው

ዘላለም ቀድሰው

በአባት ያሬድ ዜማ

ትውልድ እስኪነቃ ትውልድ እስኪሰማ

በእመ አምላክ እንዘምር

እግዚአብሔር እንዲምር

ተመስገን አባተ

**በግል ስነ ጽሁፍ**

**ምሽት የገባ**

10/09/200 ዓ.ም

## ጴጥሮስ ያቺን ለአት

ሰማዕቱ ቅዱስ ጴጥሮስ ቀዳማዊ ፋሽስት ኢጣሊያ ሀገራችንን ወሮ በቀኝ ግዛት ቢገዛን እምነታችንን ካቶሊካዊ አገዛዙን ፋሽስታዊ ሊያደርግ በሮማ ጳጳስ መሳቲሪያውን አስባርኮ የንፁሃንን  ደም ሲያፈስ ቅድስት ሀገራችንን ሊወርስ በተመመ ወቅት የሃገራችንን በባዘድ መያዝ አናይም መሬታችንን አሳልፈን አንሰጥም ሉአላዊነታችንን አናስደፍርም ያሉ የሀገራችን ጀግኖች አርበኞቻችንን አይሂችሁ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ቅድስት ሀገር ኢትዮጲያን እንጂ የኢጣሊያውያን አይደለችም በሚል ቃል አርበኞቻችንን እያበረታቱ ሁሉም ኢትዮጲያ በጸሎት እግዚብሔርን ከመጣጠብን ጠላት ይገላግለን እንዲማጸነን እያሰባሰቡ እያሉ በፋሽት ኢጣሊያ ታድነው በጭካኔ በጥይት ተደብድበው በሰማእትነት እንዲደበደቡ ተደርገዋል ። እኛም ይህን ክስተት የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ በምግብ ያስቡት የነበረውን ጉዳይ ጥበባዊ ሆነ የግጥም አገላለጽ ይዘን ቀርበናል ።

አየ ምነው እመ ብርሃን ኢትዮጲያን ጨከንሽባት

ምነው ዋንሽን ረሳሻት

እስከመቼ ድረስ እንዲህ ሙቀትሽን ታጠቂባት

ልቦናሽን ታዘሪባት

ፈተናዋን ሰቀቋዋን ጣራን ይበቃል ሳትያት

ከባንቺ እኮ ማንም የላት

አውሮፓ እንዲሁት በፋሽስት ነቀርሳ

ታርሳ ታምሳ በስብሳ

ሂትለራዊ እባጭ ጫንጫዋን እን ኮረብታ ተጭኗት

ቀና ብላ እውነት እንድታይ አንገቷን ቁልቁል በምዘሂት

ነፍሷ ድጦ ያስበረከካት

ስልጣኑን ኩኩን መጽአጉናት

እና ፈርቼ እንዳልባክን ሲርቀኝ የሀይልሽ ውጋገን

አንቺ ከአጠገቤ ስትራቂ በርታበይኝ እመ ብርሃን

ቃል ኪዳን እንዳልረሳት እንዳልዘነጋት ፈኢትዮጲያን

አዎን ብቻዬን ነኝ ፈራሁ

እሸሸግበት ጥግ አጣሁ

እማማ ኢትዮጲያን መንፈሴ ተፈትቶ እንዳይከዳት ሰጋሁ

አዋጅ የምስራች ብዬ የትብት ምግቤን ገድፌ

ከእናቴ ማህጸን አልፌ

በኢትዮጲያ ማህጸን አልፌ

ከአፈር አጥንቴን ቆፍሬ

ደሜን ከደሟ አንጥሬ

ከወሏ ወሏን ቀፍፌ

በህጻን እግሬ ሄድባት በህልም አለም ክንፍ

እረኝነቴን በስሏላ በምድር ላብ አሳልፎ

ከጫጨትና ከጥጃ በምድር ላብ አሳልፌ

በጋው የእረኛ አደባባይ ክረምት እንደ ወዝ ፈሳሽ

በገጠር የደመና ዳሰሳ በገዱሉ ሸሽለቆ አዳራሽ

በቆቅና ከሚዳቋ ከዝግራ ጠረን ከተከሻ

ከወንዝ አፋፍ ጠርጎ ዝላይ ውርወራ መጠንጠልሽ

ከፍልፍል ጋር ሩጫ ከገጥሞ ከቀበሮ ድብብቆሽ

ከናዳ ጫፍ ስር አጨደ ላግት ላሜት ትንሽ ግተሽ ›

ለጥጃዬ የሌት ግርዶሽ

ለጥማድ በሬዎች ራት ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ

ለግልገሌ ከአውራ ከለል

እማሳው ስር ጎጆ መትከል

ለጸሃይ የሸላ ጠለል ለዝናብ የነሳ ጠበል

ውሎ የንብቀፍ ማሰስ ያበበ እንቡጥ ሲፈነዳ

የግጦሽ ስር ሊለመልም ሲሰማሩ ሰደድ ሜዳ

አዝመራው ጠል ኮንበል ሲል ከብቱ ለወራ ሲነዳ

ፈገል ግልቢያ ሰሸመጥ ከወፎች ዜማ ሲቀዳ

ልቤ በንፋስ ተንሳፎ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ

ያቺን ነው ኢትዮጲያ የሞላት

እመ ብርሃን ረሳሻት

የእመቤቴ ማርያም ተማጽኔሻለሁ በካሴት ይከፈታል ከውስጥ

ያቺን የልጅነት ምስራች የህጻንነት ብስራት

የሳቅ የፍንዳቅ ዘመን የሞኛት የተስፋ ብጽእት

ያቺን የልጅነት እናት

አዛኝቷ እንዴት ብለሽ ጥርስሽን ትነክሻት

በሜን በስምሽ ሰይሜ ባገልግሎሽ ስዋትት

ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት ከጓድ ቤት እምጽህፍት

ካንቺ ተጎራኝታ እድሌ ካንቺ ተቆራለች ነፍሴ

ከቀረፋ ደረጃ ሰላም ከቤቱልሄም ቅዳሴ

እኮ ቀፎ ዳቦ ለብሶ

ቅኔ ዘርፎ ግስ ገጽ

መቅደስ አጥኖ ማህሌት ቆሞ

እመ ብርሃን ጽላት ነፍሴ ላይ እንደ እሳት ታትሞ

የመናኒው ያባ ተድላ ረድእ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ

ህይወቱ እምነት ንሽን ጽንስ

ስጋ ፈቃዴን ታግሶ

ለህንጻሽን መዲና ቆሞ ሊክብርሽ ድባብ ሞሰስ

ሰሜን በስምሽ ሰይሜ ሆናሽን የእምነቱ ፋኖስ

ለዋዜማሽ ግሽን ማርያም ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ

ስሮጥ ወንበሩ አኖርሽኝ በአንበሳው በቅዱስ ማርቆስ

ታዲያ ዛሬ ኢትዮጲያ ስትወድቅ ከሞት ሰጪኝ ለፍርሃት ጦስ

ምነው በረኝነት እድሜ እይኔን ጎጠጎጣት የለሮስ

የጋኔን ጥበብ አንሳ ከንፎ ወርዶ በጨለማ ደርሶ

ባክሽ  እመብርሃን ይብቃሽ ባክሽ ምስለ ፍቁ ተወልደ

ጽናት ስጪኝ እንድካፊል የኢትዮጲያን ፍዳ

ከነካሳት መርዞ እንደቀድሞስ ከነደደችበት ትእቶን

የእሷን ሞት እኔ እንድሞት ገላዋገላዬ እንዲሆን

እም ጸናበት ልብሴ አጣሁ

ህጻን ሆኜ የእርግብ ጫጩት አንዳንዴ ረሃብ ሲያደክማት

ችጋር ከጎም ገፍቶ እዛፍ ገርጌ ሲጥላት

እናቷ በርራ ደርሳላት

በአክናፏ መቀት ታቅፋት

እፍ እያለች ግንባሯ ላይ ህይወት ስትተነፍስባት

ወዲያው ነፍስ ትዘራለች

ኧረ . . . . ብር . . .. .ትር ትላለች

ባክሽ አንቺም አትራቂኝ

እመ ብርሃን እናቴ ትንፋስሽን እፍ በይብኝ

ጽናትሽን እፍ በይብኝ

ወይም ያቺን የምትጽዋጥላዋ ነፍሴን ካፈናት

እንዳልጠጣት አሳል ፊያት

መራራ ክንፏን ገንጥለሽ ቀጠሮ ቃሏን ግደፊያት

አለበለዚያ ምጽናትሽን ስጪኝ ልጠጣው ኪዳን ውሉን

የእኔ ፈቃድ እምነትሽ ነው ያቺን ፈቃድ ብቻ ይሁን

እንደ ጳውሎስ እንደ ጸና በፍርሃት እንዳልታሰር

በየእለቱ ሞቱ እንዳይነጥፍ

ቃልሽ ህሊናዬን ድብ በሀይልሽ በህዌ ሴይረፍ

ፍርሃት ቢረብብኝም አንቺ ካለሽኝ አልሰጋም

ኩርምት ብዬ እችልበት እሸሸግበት አይጠፋም

የግማደ መስቀል ጉጥ እታገስበት አላጣም

አንቺ አጽናኝኝ እንደጸናበት

አለዚያም ብቻዬን ነኝ ኢትዮጲያም አላንቺ የላት

አስርጪበኝ ተዕምነት ቋንቋ  ለስጋዬ አጣማጅ አቻ

ለጭንቀት መቀነቻ

አዎን ብቻዬን ነኝ ፈራሁ

እሸሸግበት ጥግ አጣሁ

እምጸናበት ልብ አጣሁ

እንቅልፍ ነው ሚያስወስድህ

ዝም አልኳቸው ዝም ይበሉኝ

ትቻዋለሁ ይተውኝ

አልነካቸውም አይንኩኝ

ብለህ ተገልለህ ርቀህ

እውነት ይተወኛል ብለህ

እንዴት ተስፋ ታደርጋለህ

ተስፋ አድርገህ ምን ልትሆን ወይስ ተስፋው ምን ሊሆንልህ

እንቅልፍ እንጂ የሚወስድህ

አልጠራቸውም አይጥሩኝ

አይንኩኝ ስሜን አይጥሩኝ

የተወጋ በቅቶት የወጋ መች እንቅልፍ አለው

የጅመሩን ካልጨረስከው

የተበደለ ቢችልም

ሲሸሸግም ቢደበቅም

የበደለ ዝም አይልም

እንዴት አስችሎት ዝም ይበል ለፍልፎ ከማስለፍለፍ

አይደል እንዴ የእሱ ቤዛ የበደሉ ጥቅም የግፍ

ሰላም መንሳት አይደል ትርፉ

ወስብሀት ለእግዚአብሔር

# ማን አልሽ እናት አለም

ለክብርሽ  የሚተጋ

ለአንችነትሽ የሚዋጋ

ቃልሽን የሚያከብር

ክበርሽን የሚዘክር

በአደባባይሽ የጸና . . . .በማህጸንሽ ጸንሽ የሚኖር

ለአንቺ ብሎ የተጋደለ

ለጥቅማ ጥቀም ያልታዘዘ

እናቴ ብሎ የተማጸነሽ

ማዕድ ያልበላ ከጠላቶችሽ

በልጅነት ያላሳፈረሽ

ማን አለሽ እናት አለም

ለአንቺ የሆነሽ በዚህ አለም

ቃል ቃል ብሎ የጸና

ጥሎሽ ያልኮበለለ ወደ አለም እንደገና

ደማስን ያልሆነብሽ ሚስጥርሽን

ለአንቺ ተቆርቁሮ ከአንቺ የወገን

እኮ ማን አለሽ ንገሪኝ

እኔም ዝም ልበል አልናገር ዳግመኛ

ግን --------- ድሮ ያኔ አባቶችሽ

ፍቅር ያላቸው አንቺ ነሽ

---

---

አዋጅ ብለው በመለኮት ክብርሽን ሲናገሩ

ባልሰማ ሲያሰው ላልተማረ ሲያስተምሩ

ክብርሽን ከፍ አድርገው ለአለም ሲናገሩ

የማንነትሽን ምስጢር ሳይደብቁ

ጥኡም ዜማሽን ላለወቀ ሲያሳውቁ

ነበር የኖሩትን የጥንቶች

ከልብ ያወቁት አዋቂዎቹ

ዛሬ ግን . . . .ያንን መሳዮን

ግን ያንን ያልሆኑ --------

ከላይ ለብሰው ------

በውስጣቸው ግን ----------

ልጆች ብለው ---------ጸሬችን ለብሰው

የክብር ካባሽን ደርሰበው

ምክራቸውን  ያደረጉ ጠላት

ውስጣቸውን የሞሉት የካዱት

እምቅ ሀብትሽን ------

ያቺን መስለው ያቺን ያልሆኑ

አሉ ከሀዲ --------

ታዲያ እናቴንም ዝም አልሽ

እስኪ ንገሪኝ ሚስጥርሽን

እኔም ልብ

-------------------------

ያቺን ነን ያሉ ልጆችሽ ----------

ሀብትሽ ተሟጠሽ አጽምሽ ቀርቷል

በአስመሳዮች ተከበሽ

---------- ልጅ አባቢ ቢለኝ

አፌን ዳባ ዳባ አለኝ ------ እንዲሉ አበው

ዛሬም ዙሪያሽን ከበው እማማ ይሉሻል

ግን ልጆችሽን አይደሉም ----------ዋሽተውሻል

በአለም የምትታወቁበትን

የሚያብራ ቅረሳሽን አርፈውሻል

ቃል አግኝተሽ ዝም አልሽ

ቤተ ክርስቲያን አሞ ልጇ ዝም ብያለሁ

ቃል ለምድር ባሰማ

ለአንድ አምላክ ሰጥቻለሁ

ምንም እናቴ ዝም ማለትሽ

ምልሽን የሚጠብቅ ሚስጥር የሚያዝ

አንድ ልጅም አላፈራሽ

ልጆችሽ ነበሩኝ

---

ፍቅር ያላቸው ለእኔነቱ

የሚዋሹኝ በማጀቱ

ልጆችማ ነበሩኝ

በአደባባይ ሰሜን ያሰጠን

ዛሬ ግን ብቸኛ ነኝ ተክብቢያለሁ በሌባ

ወልደ እንዳሎ ለደሃ ሆኛለሁ ልጅ አልባ

ከማእዴ አብረው በልተው

ቤቴን -----ቤተ ብለው

ላይክዱት ቃል ገብተው

የዘላለለም ልጅነትን ከእኔ ዘንድ ተቀብለው

ዛሬ ሸሹኝ -----

አውቀው እነደዳለወቁ

ሚስጥሬን አባኮት በእኔ ተሰቁ

ለአደባባይ አጋለጡኝ በገበናዬ ተሳቀቁ

ድሮ ድሮ በልጆቼ

ስለድሮው ተካብረቱ -----ተደስቼ

ስለ ድሮው በጫውትህ

በሀሰት ትሞላለህ

በባህር ቤት ----------

በየሀገሩ ቅዱስ ጳውሎስ

በበረሃ እየዞሩ

ስለ እኔ ሊናገሩ

ባላወቀ ሲያስተምሩ

ተጨፍጭረው ሲያስከብሩን

እናታችን አይዞሽ ሱሉኝ

ስለ እኔ ሲወግሩ

ተዘቅዝቀው ሲሰቅሉት

ጥርሳቸውን ሲያረግፉ

አንገታቸውን ሲሰይፉ

ጽህማቸወን ሲነጫቸው

የጥፊ  አበላ ሲያወርዱባቸው

ቃላቸውን አከበሩ

በነፍሳቸው ህይወት ሆነው በስጋቸው ተቀበሩ

ዛሬ ግን -----አዎ ዛሬ ግን

ታዲያ ዛሬ ምን ሆነሻል

አንገትሽን ደፍተሻል

አዝነሻል --------

ቆዝመሻል

በጥቁር ላይ ጥቁር ላብ በለሻል

የሀዘን ካባ ደርበሻል

---

በዝማሬ ያሸበረቀው አውደ ምህረት

የያሬድ ጥኡመ ዜማ የሚፈስበት መቅደስሽ

ምዕመናን እን ክዋክብት የፈሰሱት ግቢሽ

ምነው ዛሬ ጭር አለ

ቅኔ ማህሌት ጎደለ

ግቢሽን ያደመቁት

እነደ ክዋክበት የፈሰሱን

---

ለአንችነትሽ የተጋደሉ

ያመየሻቸው ልጆቼ ብሌን

እንዳይደርስባቸው አብልል

እንዳይጠማቸው አጠጥላኝ

ወደምን ገቡ ምእመናኖችሽ

በመቅደስሽ የሚራነው የጌታ ቃል

ታጅቦ በከበሮ በጸናጽል

ጥንግድ በለበሱ በካህናቱ

ለአካባቢ የሚበቁ ማህጠንቱ

ለሀገር ፈውስ የሚሆነው ጸሎቱ

ለምነድን ነው የማይሆነው እነደ ጥሉ

የያሬድ ጥኡም ዋዜማ ወዙ

እዝል አርፈው ግእዙ

የተሰጠው ባአ ዋፍቱ

አንቺን ስለከበረው በህይወቱ

ቅዱስ ጳውሎስም እነዳለው

እለት እለት የሚያስጨንቀው

የስጋ ጉዳይ አልነበረም

ሀገር ለሀገር ያንከራተታቸው

በአደባባይ ------

ለአንቺ ነበር ቅዱስ ጴጥሮስ

ተዘቅዝቆ -----

ታዲያ ላሬ ያሆኖቹ

አውቀን ያሉት አዋቂዎች

ከማን ሰው ከየት አመጡት

ተራ ህንጻናትና ድንጋይና ያሉት

እስኪ አስረጅኝ ከማን ማሩት

ዳሩ ----------

ይህንን ቢሉ አይደን ቆሞ

ከመሪው ዛፍ ወይን አይለቅምም

በቤትሽ ያሉት ምን ስይልሽ

ዙሪያሽን ከባው በዛግዙሽ

---

የተገዙ በስጋቸው

የዲያብሎስ ፈረሰኝ

ዲያብሎስ ያሰለጠናቸው

ለአገልግሎት ሳይሆን ያደሩ ለጥቅማቸው

እነሱ ጠፍተው ሰው የማያጠፉ

ብቻ ስንቱ ይወራል

ብዙ ቢያወሩት ሆድ ባድ ያቅፋል *-------- አሉ አበው

በደሙ የመሰረታት

በቃሉ ያጸናሽ

ህያው አምላክ አንቺ ይሁን

እርሱ ይሰጠን ደጉን ዘመን

የህዝብሽን ልብ መልስ

ቤትሽን እንዲሆን ፍቅር

ይዘንልን እግዚአብሔር

እኔ ግን ቃል ልግባልሽ

ላልናወጽ ላልክድሽ

ይፋ ቢያይል ሲወርድ መብረቅ

ልተባበር ከመናፍቅ ይኸው ገባሁልሽ

አውልቀያለሁ ቁር ልብ ሰሽን

ነጭ ካባ ላጎናጽፍሽ

ልጆችሽም ቃል ----------

ይኸው ከጎንሽ ቆመው በዛሬ ቃልን ገብተዋል

ድር ቢያድር አንበሳ ያድር  ነውና  ተረቱ

ዛሬ እንተባበር እንድናቅ ከጥፋቱ